በኀ. ኢ.ት ሕ.ወ መንግሥት

የሕዝብና የቤት ቆጠራ ኮሚሽን

የእስታቲስቲክስ፡ ጠ/ጽ/ቤት፡
ቤተ፡ መጻሕፍት፡
C. S. O Library

# የ1976 ዓ.ም. የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ

# የቆጣሪዎች መመሪያ-ገጠር

አዲስ አበባ
የካቲት 1976 ዓ.ም.

ዓምድ — 16 ማንበብና መጻፍ የማይችሉ የሚችሉ ............ 71
ዓምድ — 17 ብሔረሰብ ........................ 72
ድምር ........................ 72
ጠቅላላ ድምር ........................ 72
ዓምድ — 18 ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት .................. 73
ዓምድ — 19 ጠቅላላ የመኖሪያ ቤቶችና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት .................. 73
ዓምድ — 20 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ስም፣ ፊርማና ቀን ... 73

<u>ስለ ቆጠራ ቦታ ካርታ ዝርዝር መግለጫ</u> .................... 74

የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም ........................ 75
ዕዝል 1 ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር ................ 85

ዕዝል 2
2.1 የቤት የቤተሰብና የድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ፤ ቅጽ 1 - - - - - 88
2.2 ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ፤ ቅጽ 2 - - - - - - 89
2.3 በቆጠራ ጊዜ የቆጣሪ ዕለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ፤ ቅጽ 3 - - - - - - 90
2.4 የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ፤ ቅጽ 4 - - - - - 91
2.5 የ1975 የኢትዮጵያ የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ—ገጠር - - - - - - - 92

ሠ/ መዝገቢው በቀጠረው ቦታ በሜን ምዕራብ ከሚገኘው መንደር /ዞን/በመነሳት ወደ ምሥራቅ ሥርዓት ባለው መንገድ በመጓዝ እያንዳንዳቸውን ቤቶች ቤተሰብና ድርጅት በቅደም ተከተል መመዝገብ፤

ረ/ መዝገበው የሚከናወነው በያንዳንዱ መንደር /ዞን/ የሚገኙትን ቤቶች ቤተሰብና ድርጅቶች መዝገብ ከጨረሰ በኋላ ወደሚቀጥለው መንደር /ዞን/ በመሸጋገር ይሆናል፤

ሰ/ መዝገበው የተጀመረበትን ቦታ ለማመልከት በቆጠራው ካርታ ከመነሻው ላይ የ"x" ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል ። ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ በካርታው የ"x" ምል ክት ከተደረገበት ቦታ መጀመር ያስፈልጋል፤

ሸ/ በቆጠራ ካርታው የ"x" ምልክት ከተደረገበት የመጀመሪያ ቤት በመጀመር በቀዩ ጠመኔ በቤቱ በር ከፍ ብሎ በስተግራ ባለው በር ተገ ወይም በር ከሌለው ከመቼ በሆነና ዘናብና ልጆች ሊያጠፉት በማይችሉበት ቦታ ተከታታይ የቤት ተራ ቁጥር ይሰጣል ።

ቀ/ መዝገብ ተጠናቀቀ ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ በካርታው የ"x" ምልክት ከተደረገበት የመጀመሪያው ቤት በመጀመር ለተቆጠረ ቤት የተቆጠረ መሆኑን ለማመልከት በበማያ ጠመኔ በቤቱ ቁጥር አንፃር የ"x" ምልክት ይደረግበታል ።

በ/ መዝገበው በሚካሄድበት ጊዜ በጫካ ውስጥ የሚገኙ, በቀላሉ ሊታዩ የማይችሉ ቤቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ጠይቆ ማግኘትና መመዝገብ ያስፈልጋል፤

ተ/ የመዝገበው ሥራ ተጠናቀቀ የሚባለው በቆጠራው ቦታ ውስጥ የሚገኙት ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች በሙሉ ሲመዘገቡ ነው ። በገጠር በቆጠራ ቦታ የመዝገብ አፈጻጸም ሥርዓት በገጽ 10 በሚቀጥለው ምስል እንደተመለከተው ይሆናል ።


## የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ቅጽ አሞላል መመሪያ፤

ክፍል — 1 የአከባቢ መለያ

ከዓምድ 1 — 8 ባሉት ዓምዶች የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት የአከባቢ መለያ መረጃ ይሞላል ።

ክፍለ ሀገር — አርሲ
አውራጃ — ጭላሎ
ወረዳ — ኮፈሌ
ገ/ማ/ — ቆማ አፉማ


የሊ/መዝገቡ ስም — ከሾ ጉዮ
የቤተሰብ ብዛት — 187
የቆ/ቦታ ቁጥር — 54-02
ግምታዊ ስፋት — 3.5 km²
የመቆ/ቦታ ቁ — 15




የቆጠራ ቦታ ካርታ — በገጠር

ክፍለ ሀገር — አርሲ
አውራጃ — ጭላሎ
ወረዳ — ኮፈሌ
ገበሬ ማ. — ቀማ ኢፋሞ

የሊቀ መንበሩ ስም — ከቾ ጉዬ
የቤተሰብ ብዛት — 187
የቆ. ቦታ ቁጥር — 54-02
ግምታዊ ስፋት — 3.5 km²
የመቆጣጠሪያ ቦታ ቁ. — 15




መስፈርት 1:50,000

መግለጫ

- የገ.ማ. ክልል
- የቆጠራ ቦታ ክልል
- የእግር መንገድ
- ወንዝ
- ደረቅ ወንዝ
- መንደር
- ሳር ክዳን ቤት

በገጠር ቆጠራ ቦታ የቤት የቤተሰብና የድርጅት ምዝገባ አፈጻጸም ሥርዓት

ዓምድ—1 <u>ክፍለ ሀገር</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ስም ይመዘገባል ።

ዓምድ—2 <u>አውራጃ</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት አውራጃ ስም ይመዘገባል ።

ዓምድ—3 <u>ወረዳ</u>

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ወረዳ ስም ይመዘገባል ።

ዓምድ—4እና 5 <u>ከተማና ከፍተኛ</u>

ይህ ዓምድ አይሞላም ።

ዓምድ—6 <u>የመቁጠሪያ ቦታ</u>

ቤተሰቡ የሚኖርበት የመቁጠሪያ ቦታ ኮድ ቁጥር በዚህ ዓምድ ከ11—12 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል ።

ዓምድ—7 <u>የገበሬ ማኅበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ</u>

ቤተሰቡ የሚኖርበት የገበሬ ማኅበር ወይም ሠፈራ ጣቢያ ስም በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተመዝግቦ ኮድ ቁጥር በዚህ ዓምድ ከ13—15 ባሉት ኮለሞች ይሞላል ።

ዓምድ—8 <u>የቀበሌ ቦታ</u>

ቤተሰቡ የሚኖርበት የቀበሌ ቦታ ኮድ ቁጥር በዚህ ዓምድ ከ16—17 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል ።

<u>ማሳሰቢያ</u>

ለመቁጠሪያ ቦታ፣ ለገበሬ ማኅበር ወይም ሠፈራ ጣቢያ ለቀበሌ ቦታ የሚሞላው ኮድ በቀበሌ ካርታ በቀበሌ ቦታ ማኀደር ለነዚህ ክፍሎች በተሰጠው ኮድ መሠረት በማደረግ ሲሆን ይህንኑ ኮድ በተገቢው ዓምድና ካርድ ኮለም ማወራረስ ያስፈልጋል ።

ገበሬ ማኅበሩ ወይም ሠፈራ ጣቢያው በካርታ ያልተሸፈነ ከሆነ ስሙ ብቻ በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይጻፋል፡፡

## ክፍል — 2 የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ሁኔታ

### ዓምድ—9 የቤት ተራ ቁጥር

በቆጠራው ቦታ ለሚገኙ ቤቶች እንደ አመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል ተከታታይ ተራ ቁጥር 001፣ 002፣.....ወዘተ በማለት ቤቶቹ ተመዝግበው እስከአለቀ ድረስ በዚህ ዓምድ በካርዱ ክለም 18—20 ይሞላል ። እነዚህ በካርዱ ክለም 18—20 የተመዘገቡት ተራ ቁጥሮች በቤቱ በር ከፍብሎ በስተግራ ባለው ጥግ ወይም በር ከሌለው አመቺ በሆነና ዝናብና ልጆች ሊያጠፉት በማይችሉበት ቦታ በቀይ ጠመኔ መጻፍ ያስፈልጋል ። በአንድ ቤት ሁለትና ከዚያ በላይ ቤተሰቦች /የቤተሰብ ትርጉም ለዓምድ 10 በተሰጠው መግለጫ ተገልጿል/ ከኖሩበት የነዚህ ቤተሰቦች ኃላፊዎች በዓምድ 17 በየተራ በሚመዘገቡበት ጊዜ የቤቱ ተራ ቁጥር በዓምድ 9 ተደጋግሞ መጻፍ ይኖርበታል ። በሌላ በኩል ደግሞ ፎቅ በሆነ ቤት ውስጥ አራት መኖሪያ ቤቶች ካሉ ለአራቱም የቤት ተከታታይ ተራ ቁጥር በዓምድ 9 መስጠት ያስፈልጋል ። በሌላ አነጋገር በአንድ አጥር ግቢ አንድ ቤተሰብ የሚኖርባቸው ከአንዱ ቤት በላይ ቢኖሩ አንዱ የቤት ተራ ቁጥር ለዋናው ቤት የሚሰጥ ሲሆን ከአንድ በላይ ቤተሰብ የሚኖርባቸው ከሆነ ግን ለያንዳንዱ ተከታታይ የቤት ቁጥር መስጠት ያስፈልጋል ።

ዓምድ—10 የቤት ቁጥር

የቤት ቁጥር በዓምድ 10 ከመመዝገቡ በፊት የቤት፣ የመኖሪያ ቤትና የቤተሰብ ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

ሀ. ቤት

ቤት ማለት በአሠራሩ ተለይቶ "ራሱን የቻለ" ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድርጅት ብቻ የሚያገለግል ነው።

የቤቱ አሠራር የተለየ ነው

የሚባለው ፊያውን በግድግዳ፣ በአጥር ገቢ...ወዘተ የተከለለ ሆኖ ጣራውም በክዳን የተሸፈነ በመሆኑ በውስጥ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፣ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመለየት የሚያስችል ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በሰጠራ፣ በፕላስቲክ፣ በካርቶን፣....ወዘተ ግድግዳው የተሠራ ወይም በበና ጣራው በፕላስቲክ ክዳን የተሸፈነ ሆኖ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግል ቤት ሊያጋጥም ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንፃር ቢታይ ቤት ስለሆነ እንደቤት ይወሰዳል።

<u>የቤቱ አሠራር ራሱን የቻለ ነው</u> የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ ደረጃ፣ መሬት.... ወዘተ የራሱ መግቢያና መውጫ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተላለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ባይሆን በቀጥታ በራሳቸው ቤት መውጫ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው።

ለ. መኖሪያ ቤት

መኖሪያ ቤት ማለት ሙሉ በሙሉ ሰዎች የሚኖሩበት ወይም በከፊል እየኖሩ በቀረው ሌላ ተግባር ለምሳሌ ንግድ፣ ሽመና፣ የእንጨት ሥራ...ወዘተ የሚያከናውኑበት ቤት ማለት ነው። የመኖሪያ ቤት ሲባል መኖሪያ ተብሎ የተሠራ ወይም የተዘጋጀ ወይም ለመኖሪያ ተብሎ የተሠራ ወይም የተዘጋጀ ባይሆን በቆጠራው ጊዜ እንደ መኖሪያ የሚያገለግል ሲሆን ይችላል።

ሐ. <u>ቤተሰብ</u>

ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማድ ቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡ የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባል ወይም የሚስት አባት፣ እናት፣ እህት፣ ወንድም፣.... ወዘተ ሲሆኑ በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱት ሌሎች የቤተሰብ አባላት ናቸው፡፡ የቤተሰብ አባላት በቤት ሠራተኛነትና በዘበኝነት የሚያገለግሉትንም ይጨምራል፡፡

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል፡፡ ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘበኞች፣ ጥገኞች፣... ወዘተ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ፡፡ ነገር ግን ቆጠራው ከሚፈጸምበት ቀን በፊት ቤተሰቡን ትቶ ለእንግድነት ወደ ሌላ ቤተሰብ በመሄዱ እዚያ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን በሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው፡፡

ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን /የቤት ሠራተኞች.... ወዘተ/ ሊያጠቃልል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ /አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ከአሉት/የየሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው... ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩ፣ ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፣ በቅድሚያ ካገባት ሚስቱ በስተቀር እያንዳንዳቸው የሰውየው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ እንዳላቸው ሆኖ መቆጠር አለባቸው፡፡ ባልየው ደግሞ በቅድሚያ ካገባት ሚስቱ ጋር እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራል፡፡

ዓምድ — 12 <u>የቤቱ አገልግሎት</u>

በዚህ ዓምድ ከዓምድ 9—11 የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚ ሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል፡፡ የአገልግሎት ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡

1 = ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ
2 = ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት
3 = ለሆቴል
4 = ለሆስፒታል
5 = ለሌላ ጋርዮሽ
6 = ለሌላ ድርጅት ብቻ
7 = ያልተያዘ
8 = በመሠራት ላይ ያለ

ከዚህ ቀጥሎ ለእያንዳንዱ የቤት አገልግሎት ዓይነት ትርጉምና የአመዘጋገቡ ሁኔታ ተብራርቷል፡፡

1. <u>ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የዋለ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ" ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ የኮድ ቁጥር "1" በካርዱ ኮለም 28 ይሞላል፡፡

2. <u>ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ ቤተሰብ መኖሪያና ለድርጅት" ተብሎ ይመዘገብና ኮድ "2" በካርዱ ኮለም 28 ይሞላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የድርጅት ትርጉም ተሰጥቷል፡፡ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚለው ሆቴል፣ ሆስፒታልና ሌላ ጋርዮሽን አይጨምርም፡፡

## ድርጅት

ድርጅት ማለት በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ የሶሻል ወይም የኢኮኖሚ ተቋም ነው፡፡ ይኸውም የማምረቻ፣ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞችን ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ ጫማ፣ ሳሙና፣ ጨርቃ ጨርቅ፣.... ወዘተ አምራቾች፣ የጫማ አደባት፣ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሕግ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት እና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ የሚያካሂዱትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

ከላይ በተሰጠው የድርጅት ትርጉም መሠረት የቤቱ አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚባለው በአንድ ቤት ውስጥ የቤተሰብ አባላት እየኖሩበት እዚያው ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት የድርጅት ዓይነቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተግባራት ቢያከናውኑበት ነው፡፡ ይኸውም ለምሳሌ፡—

ቤቱ ለመኖሪያና ለመጠጥ መሸጫ /ጠላ፣ ጠጅ ሌሎች መጠጦች/
" " ለምግብ መሸጫ
" " ለሸመና
" " ለንግድ /ኪዮስክ/
" " ለሸክላ ሥራ
" " ለብረታ ብረት ሥራ
" " ለጫማ ሥራና ጥገና

በቤቱ ውስጥ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ባለቤቶች የማይኖሩበት ቢሆንና ነገር ግን ሠራተኞች የሚኖሩበት ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት ተብሎ ይመዘገባል፡፡

## 3፡ ሆቴል

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለሆቴል ብቻ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለሆቴል ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ በኮርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 3 ይሞላል፡፡ በሆቴል ውስጥ በቤተሰብ መልክ የሚኖር እንደ ሆቴል ነዋሪ እንጂ እንደ ቤተሰብ አይቆጠርም ፡፡

ሆቴል፡— ማለት የምግብ፣ ወይም የመጠጥ ወይም የመኝታ አገልግሎት ወይንም ሁሉንም የሚሰጥ ድርጅት ነው ፡፡

ሆስቴል

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለሆስቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሆስቴል" ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ በካርዱ ከለም 28 የኮድ ቁጥር "4" ይሞላል።

ሆስቴል፡— ሆስቴል ማለት ብዙ ሰዎች ከመደበኛ ቤተሰብ አኗኗር ወጪ በአንድ ቤት ወይም ቤቶች በአንድነት ከየኖሩ በቤቱም ያሉ ትን መገልገያዎች ማለት ውሃን፣ መብራትንና ሌሎች አገልግሎቶችን በጋራ ወይም በኅብረት የሚጠቀሙበትና በአንድ ድርጅት ሥር የሚተዳደሩበት የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራ ነው።

5. ሌላ ጋርዮሽ

ሌላ ጋርዮሽ የሚባሉት ከሆቴልና ከሆስቴል /በስተቀር ሌሎችን የጋርዮሽ መኖሪያ ሥፍራዎችን በሙሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው።

ይኸውም፡— ወህኒ ቤቶች፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶች፣ ሕፃናት ማሳደጊያ፣ ሆስፒታሎች
የወታደር ካምፕ፣ ያረጁ ሰዎች መጦሪያዎች፣ /ፖሊስ ጣቢያ እሥር ቤት ካለው/፣ የፀበል ማረሚያዎች፣ አደባራትና ገዳማት፣ የሠራተኛ ካምፖች፣.... ወዘተ ናቸው።

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከሆነ የቤት አገልግሎት "ሌላ ጋርዮሽ" ተብሎ በዓምድ 12 ይመዘገብና በካርዱ ከለም 28 የኮድ ቁጥር 5 ይሞላል።

6. ሌላ ድርጅት

ሌላ ድርጅት የሚባሉት ሆቴልን፣ ሆስቴልንና "ሌላ የጋርዮሽ" መኖሪያዎች ባይጨምሩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የሚያጠቃልሉ ናቸው።

ይኸውም፡— የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የማምረቻ ድርጅቶች፣ የንግድ ተቋሞች፣ ቤተ ክርስቲያኖችና መስጊዶች /የግለሰቦችን የጸሎት ቤቶች አይጨምርም/፣ መጠጥ ቤት የሌለው ቡና ቤቶች፣ መጠጥ ቤት የሌለው ገርበሬዎች፣ ጋራዥ፣ መጋዘን፣ ትምህርት ቤት፣.... ወዘተ

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ሌላ ድርጅት" ተብሎ በዓምድ 12 ይመዝገብና በካርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 6 ይሞላል፡፡

## 7. ያልተያዘ

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን በሆነ ምክንያት በአገልግሎት ላይ ያል ዋለ እንደሆነ "ያልተያዘ" ቤት ተብሎ በዓምድ 12 ይመዝገብና በካርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 7 ይሞላል፡፡

## 8. በመሠራት ላይ ያሉ

በመሠራት ላይ ያለ ቤት ማለት ቢያንስ ግድግዳው የቆመ ወይም ያለቀ ወይም ጣራው ያለቀ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ተሠርቶ ያልተጠናቀቀ ማለት ነው፡፡ የሚመዘ ገበው ቤት በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ከሆነ "በመሠራት ላይ" ተብሎ በዓምድ 12 ይመዝገብና በካርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 8 ይሞላል፡፡ ነገር ግን በመሠራት ላይ ያለ ቤት በቆጠራው ወቅት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የአገልግሎቱ ዓይነት በዓምዱ ይመዝገባል፡፡ ለምሳሌ በመሠራት ላይ ያለ ቤት ለመደበኛ መኖሪያ በማገ ልገል ላይ ካለ ለመደበኛ መኖሪያ ተብሎ ይመዝገባል፡፡ እንዲሁም ለድርጅት በማ ገልገል ላይ ካለ የድርጅቱን ዓይነት መመዝገብ ነው ፡፡ ይኸውም ሆቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለሆቴል፣ ለሆስቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሆስቴል፣" ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሌላ ድርጅት" ተብሎ ይመዝገባል፡፡

## ዓምድ 13—15 ቤቱ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሌላ ,ጋርዥ ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት ቤቱ በቆጠራው ቀን ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሌላ ጋርዥ ወይም ለሌላ ድርጅት የሚያገለግል ከሆነ ነው፡፡

2 = ከብት አርባታ ብቻ /ምንም ሰብል ባያመርቱ ከብት ብቻ የሚያረቡ/

3 = ሌላ ግብርና /ዶሮ አርባታ፣ ንብ አርባታ፣ ዓሣ ማስገር፣ ከሰል ማክሰል፣... ወዘተ /

4 = ሰብልና ከብት አርባታ /ሰብል አያመረቱ አንዱ ከብት ወይም ከዚያ በላይ የሚያረቡ/

5 = ሰብልና ሌላ ግብርና

6 = ከብት አርባታና ሌላ ግብርና

7 = ሰብል፣ ከብት አርባታና ሌላ ግብርና

ዓምድ — 19 <u>አስተያየት</u>

ይህ ዓምድ ምዝገባው በሚካሄድበት ወቅት ከምዝገባው ጋር ግንኙነት ያላቸው ችግሮች/ሌሎች ሁኔታዎች ያጋጠሙ እንደሆነ ይመዘገቡበታል።

## <u>ማሳሰቢያ</u>

<u>ለሆቴልና ለሆስቴል ነዋሪዎች፣ ለሌላ ጋር ዮሽ ነዋሪዎች እንደዚሁም ቤት ለሌላቸው ግለሰቦች እንደ መደበኛ ቤተሰብ አባላት የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች መጠይቅ ይሞላላቸዋል። መጠይቆቹ በሚሞሉበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል።</u>

ሀ. <u>የሆቴል፣ የሆስቴልና የሌላ ጋር ዮሽ ነዋሪዎችን በሚመለከት</u>

በዓምድ 9 የነዋሪው ዓይነት በሚመለከት የሆቴልና የሆስቴል ወይም ሌላ ጋር ዮሽ ነዋሪ ለሚለው የተሰጠው መልስ ኮድ በካርድ ኮለም 23 ውስጥ ለተሞላላቸው በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ውስጥ የሚከተሉት ዓምዶች ወይም ክፍሎች አይሞሉም። ማንኛውም በሆቴሉ ወይም በሆቴሉ አጥር ግቢ በቤተሰብ ወይም በሆቴል የአኗኗር ስርዓት የሚኖር እንደሆቴሉ ነዋሪ ተወስዶ መጠይቁን ይሞላለታል።

## የ1976 የኢትዮጵያ የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ
## አሞላል መመሪያ

መጠይቁ አምስት ክፍሎች ያሉት ቢሆን የየክፍሉም አሞላል መመሪያ ከዚህ በታች ተመልክቷል።

### ክፍል አንድ — የአካባቢ መለያ

ከዓምድ 1—13 ባሉት ዓምዶች የቆጠራው ክልል የሚገኝበት የአካባቢ መለያ መረጃ ይሞላል።

### ዓምድ 1— ክፍለ ሀገር

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ስም ይመዘገባል። በቀራዙ በተሰጡት ኮድ ብሎኮች ኮዱ ይሰፍራል።

### ዓምድ 2 — አውራጃ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት አውራጃ ስም ይመዘገባል። በቀራዙ በተሰጡት ኮድ ብሎኮች ኮዱ ይሰፍራል።

### ዓምድ 3 — ወረዳ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ወረዳ ስም ይመዘገባል። በቀራዙ በተሰጡት ኮድ ብሎኮች ኮዱ ይሰፍራል።

### ዓምድ 4 እና— ከተማና ከፍተኛ

እነዚህ ዓምዶች አይሞሉም።

### ዓምድ 6— የመቆጠሪያ ቦታ

ቤተሰቡ የሚኖርበት የመቆጠሪያ ቦታ ኮድ በዓምድ 6 ከ16—17 ባሉት ኮድ ብሎኮች ይሞላል።

**ዓምድ 7 — የግብረ ማኅበር ወይም የሠፈራ ጣቢያ**

ቤተሰቡ የሚኖርበት የግብረ ማኅበር /ወይም የሠፈራ ጣቢያ/ ኮድ በዓምድ 7 ከ18—20 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል።

**ዓምድ 8 — የቀበሌ ቦታ**

ቤተሰቡ የሚኖርበት የቀበሌ ቦታ ኮድ በዓምድ 8 ከ21—22 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል።

**ዓምድ 9 — የነዋሪ ዓይነት**

የነዋሪ ዓይነት መደበኛ ቤተሰብ፣ የሆቴልና የሆስቴል፣ ሌላ የጋርዮሽ ቤት ነዋሪ ወይም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ መጠይቁ የሚሞላለት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ የነዋሪውን ዓይነት በመለየት ከሚከተሉት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በካርድ ኮለም 23 ይሞላል።

1 = መደበኛ
2 = ሆቴልና ሆስቴል ነዋሪ
3 = ሌላ የጋርዮሽ ነዋሪ
4 = ቤት የሌላቸው
5 = ዘላን

**ዓምድ 10 — የቤት ተራ ቁጥር**

በቤት፣ በቤተሰብና በድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ 1 በዓምድ 9 በምዝገባው ወቅት የቤት ተራ ቁጥር ተሞልቷል። በቅጽ 1 በዓምድ 9 የተመለከተውን የቤት ተራ ቁጥር በዓምድ 10 ከ24—26 ባሉት ካርድ ኮለሞች መገልበጥ ያስፈልጋል።

**ዓምድ 11— የቤት ቁጥር**

በዓምድ 11 የሚሞላው የቤት ቁጥር በቤቶች፣ በቤተሰቦችና፣ በድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ በዓምድ 10 የተመዘገበውን የቤት ቁጥር በመገልበጥ ነው። ቤቱ የቤት ቁጥር ከሌለው ዓምዱ ሠረዝ " — " ይሞላል።

እንግዶችን በሚመለከት በተለይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ስለ እንግዶች የሚጠየቁት የመረጃዎች ዓይነት ስም፣ የነዋሪ ሁኔታ፣ ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለ ዝምድና፣ ፆታና ዕድሜ ብቻ ናቸው። እነዚህም ከዓምድ 15—19 ያሉትን ይመለከታል።

## ዓምድ 15.1 — ማስታወሻ

በዓምድ 15 የተመዘገቡትን መደበኛ የቤተሰብ አባላትና የእንግዶች ሙሉ ስም ለመልስ ሰጪው ማንበብና የተመዘገቡትን ብዛት በመንገር ሳይመዘገብ የቀረ መደበኛ አባል ወይም እንግዳ ካለ በዓምድ 15 መመዝገብ ያስፈልጋል።

## ዓምድ 16 — የነዋሪ ሁኔታ

የነዋሪ ሁኔታ ሦስት ሲሆን ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፡—

1 = በእለቱ ቤት የነበረ ነዋሪ፡— የሚባለው መደበኛ የቤተሰብ አባል ሆኖ ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቤት የነበረ ናቸው።

2 = በእለቱ ቤት ያልነበረ ነዋሪ፡— የቤተሰቡ መደበኛ አባል ሆኖ ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቤት ያልነበረ ናቸው።

3 = በእለቱ ቤት ያደረ እንግዳ፡— የቤተሰቡ መደበኛ አባል ባይሆን ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቆጠራው በሚካሄድበት ቤት ያደረ ግለሰብ ናቸው።

ስለዚህ ከላይ በተሰጠው ትርጉም መሠረት የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም በዓምድ 16 በካርዱ ኮለም 32 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል።

1 = ቤት የነበረ ነዋሪ
2 = ቤት ያልነበረ ነዋሪ
3 = ቤት ያደረ እንግዳ

## ዓምድ 17 — ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና

በዓምድ 15 የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሚመዘገቡበት ጊዜ በመጀመሪያው መስመር የሚመዘገበው ሁልጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ ይሆናል። ስለዚህ በዓምድ 17 በመጀመሪያው መስመር "ኃላፊ" ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ እያንዳንዱ የቤተሰብ መደበኛ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና በተሰጠው ክፍት ቦታ ተጠይቆ ይሞላል። ለምሳሌ

## ዓምድ 18 — ጾታ

በዓምድ 15 በተመዘገቡት ግለሰቦች ስም አንጻር ጾታቸው ከተመዘገበ በኋላ በከርድ ኮለም 34 ተስማሚው ኮድ ይሞላል፡፡ ለምሳሌ የአባሉ ጾታ ወንድ ከሆነ በስሙ አንጻር ወንድ ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ በካርድ ኮለም "34" ኮድ "1" ይጻፋል፡፡ እንዲሁም የአባሉ ጾታ ሴት ከሆነ በስሟ አንጻር ሴት ተጽፎ በከርድ ኮለም 34 ኮድ "2" ይሞላል፡፡ የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ጾታዎች ሊያገለግል ስለሚችል የአባላቱን ስም ብቻ መሠረት በማድረግ ጾታቸው በግምት መሞላት የለበትም፡፡ በአንዳንድ አካባቢ ወንዶች በሴት ስም እንዲሁም ሴቶች በወንድ ስም ስለሚጠሩ ጾታ በሚሞላበት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 19 — ዕድሜ

ዕድሜ ማለት አንድ ሰው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ቆጠራው እስከተካሄደበት ቀን ድረስ ያለው የጊዜ ብዛት /ቀን፣ ወር፣ ወይም ዓመት/ ነው፡፡ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ ዕድሜ በሙሉ ዓመት በዚህ ዓምድ ይመዘገባል፡፡ ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው፡፡ ለምሳሌ የአንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት፣ ከ5 ወር ከ11 ቀን ቢሆን መመዝገብ ያለበት ዕድሜ 15 ዓመት ብቻ ይሆናል እንጂ 15 ዓመት፣ ከ5 ወር ከ11 ቀን መሆን የለበትም፡፡ የአንድ ሕፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ በዓምድ 19 በካርድ ኮለም 35—36 ባለው ቦታ "00" ይመዘገባል፡፡ እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜው 98 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ "98" ብቻ በካርድ ኮለም 35 እና 36 ይመዘገባል፡፡

ዕድሜአቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜአቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያጋጥሙ ይገመታል፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በተቻለ መጠን ለማግኘት ያለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማጤን ይገባል፡፡

ኮድ　　　　　　ብሔረሰብ

08.... ቀግ

09.... ቅማንት

10.... ቤጃ፣ በዳዊ፣ ሀዳረብ

11.... ኦሮሞ /ቱለማ፣ ኢቱ፣ ከረዩ፣ ወሎ፣ ሰሙ፣ ሌቃ፣ ገላን፣
በቾ፣ አበቹ፣ በሰሌ፣ አርሲ፣ ራያ አዘቦ/

12.... ቦረና

13.... ጉጂ

14.... አርቦሬ፣ ኤርቦሬ፣ አልዲ

15.... ጠባ፣ ሞሲያ

16.... ዳሰነች፣ ገለብ፣ ገሰብ

17.... ገዋዳ፣ ማሾሌ፣ ኩሌ /ጎበዜ፣ ወርዜ፣ አሌ/

18.... ጊዶሌ፣ ዳራሽት፣ ጋርዱላ፣ ዲራይታታ፣ ዱራቴ

19.... ኮንሶ /ካራቴ/

20.... ፀማይ፣ በማይ /ዱሜ፣ ኩዌሌ/

21.... ሲዳማ

22.... ቡርጂ ዳሪ፣ ባምባላ

23.... ጌዴኦ፣ ደራሳ

24.... ሀዲያ፣ አዲያ

25.... ከምባታ፣ ሀምባታ

26.... አላባ

27.... ጠምባሮ

28.... ቀቤና

29.... አፋር፣ ዳናኪል፣ ዳንከሌ /በለሰዋ፣ ዳሞሂታ፣
ዳሂሚላ፣ አንከለ፣ ሞዳይቶ/

30.... ሶማሌ/ ዳሮድ፣ ኢሳቅ፣ ሀውያ፣ ገደቡርሲ፣ ኢሳ/

31.... ሳሆ፣ ሻሆ /ደበሪ ሜላ፣ ዓሳዎርታ፣ ሚኒፈሬ፣ ሀዞ፣
ኢሮብ፣ ጠሩዓ/

32.... ማኦ፣ /ሕንፈሶ፣ ጋንዛ፣ ሲጎዩ፣ ገዋማ፣ ባምባሺ፣ ፈዳሽ/

33.... ኮሬ፣ አሬ፣ አሮ /ካኮ፣ሻንጋማ፣ ካሮ/

34.... ሀመር፣ በሻዳ /ሰና፣ ካሮ/

35.... ዳሜ

36.... ዲዚ፣ ማጂ

| ቦታ | ብሔረሰብ |
|---|---|

37.... የምባ፣ የማ፣ ጃንጀሮ
38.... ቤንች፣ ቤንችኛን፣ ሼ፣ ጊሚራ
39.... ከፋ፣ ከፍቾ /ጎንጋ፣ ቦሽጌር/
40.... ናኦ፣ ናዎ
41.... ሞቻ፣ ሼኪ
42.... ሸኮ፣ ሜዠ፣ ሙሳ፣ ዲርባ፣ ዲርቦ፣ ዲርቦ
43.... ሸናሻ፣ ቦሮ /ቦርቻ፣ ሽኮ፣ በሜን ሽኮ/
44.... ዶሜቴ፣ ኩሎ፣ ዳውሮ
45.... ቦንታ
46.... ባስኬቶ፣ አንጂላ፣ ሜሼሌ /ዶኮ፣ ዶሎ ዶላ/
47.... ዶርዜ
48.... ጋሞ
49.... ጋንጁሌ፣ ባጫ
50.... ጎፋ፣ ገቶ
51.... ቁጫም፣ ኳጫሞ፣ ጋዳም፣ ሀፋር
52.... ከዩራ፣ አማሮ፣ አመርቴ፣ ጊዴቻ
53.... ማሌ
54.... ማሎ፣ ዳውሳ
55.... ጨራ
56.... ወላይታ
57.... ዘይሴ፣ ዘርጉላ
58.... አይዳ
59.... ኩሮሜ፣ ቱርሜ፣ ዳሜ
60.... ኳጉ፣ ቢጉ፣ ሙጂ፣ ቶዲ፣ ኚዩኔ
61.... መኤን፣ መቀን፣ ዳይና፣ ባርኮሞ /ቦቼ፣ ቦዲ፣ ኮና፣ ሚኒት/
62.... መስንጎ፣ ማጀንግ፣ መዘንገር
63.... ሙርሲ፣ ሙን፣ ሙኒ፣ ኚሳብንግ፣ ጧማ
64.... ሱሪ፣ ጂዬ፣ ኚርማ
65.... ዜልማም፣ ባሌ፣ ዲሌ፣ ዳሰሜም
66.... ሙርሌ /አሰም ሙርሌ፣ ሶም ሙርሌ፣ ሶሎች/
67.... አኝዋ፣ አኝዋክ፣ ዩምቦ
68.... ማባን

| ኮዱ | ብሔረሰብ |
|---|---|

69.... ኑዌር፣ አቢጋር

70.... ኛንጋቶም፣ ቶርካና፣ ቡሜ

71.... በርታ

72.... ጋሚሊ

73.... ጎበት

74.... ሚቶ

75.... ኒዓሺ

76.... ፈኩንኩም

77.... ኦንቓ

78.... ገበቶ

79.... ቤኸንጉል

80.... ጀበሳዊ፣ አርቦ

81.... ኩናማ፣ ባዓ፣ ካዛን፣ ባዛ /ሶማዬሽ በርካ፣ ቢታማ፣ ኢሉት፣
ማርዓ፣ በቴት፣ በጎዓስ፣ ቲካ/

82.... ወይጠ

83.... ፈሳሽ፣ ካዩሳ፣ ቤተስራኤል

84.... ኮማ፣ ኮዎ፣ ሀያሀያ፣ መጀን

85.... ጉሙዝ፣ ጋንዛ፣ ጋንዛ /ሲስ፣ ሽዬ ኡካሁ፣ ገበጠ/

86.... ከቀማ፣ ኪማ

87.... ሽታ፣ ፎታ፣ ሳንጋ

88.... ናራ፣ በሬያ፣ ማርዓ /ሂገር፣ ቀጋሬብ ባንቶራ፣ ኮይታ፣ ኮይቻ/

95.... ብሔረሰባቸው ያልታወቀ ኢትዮጵያውያኖች

96.... ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ሰዎች

97.... ከተለያዩ ብሔረሰቦች የተወለዱ

98.... ሌሎች ብሔረሰቦች

x = ከልደት ጀምረው ያለማቋረጥ እስከ ቆጠራው ቀን ድረስ በከተማው ለሚኖሩና አዲስ ለተወለዱ ሕፃናት፡፡

0 = ከዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

1 = አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

2 = ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሦስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

3 = ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከአራት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

4 = አራት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከአምስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

5 = አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከስድስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

6 = ከስድስት እስከ 9 ዓመት ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

7 = ከአሥር እስከ 15 ዓመት ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

8 = ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ያለማቋረጥ በወረዳው ለኖሩ፣

## ዓምድ 28 የአካል ስንኩልነት ሁኔታ፣.... አካለ ስንኩል ናቸው? ከሆኑ ዓይነቱ ይገለጽ

ሲወለዱ ወይም ከተወለዱ በኋላ የበውነት፣ የአእምሮ፣ ወይም የሌላ የአካል ክፍል መበላሸት የደረሰበት ግለሰብ አካለ ስንኩል ይባላል፡፡ በአጠቃላይ አካለ ስንኩል የሚባለው ግለሰቡ የአካሉ ክፍል በመሰናከሉ፣ በመጎዳቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት ሌሎች ደህና የሆኑ ሊያከናውኑት የሚችሉትን ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን ባለመቻሉ የሲቪልና የኢኮኖሚ ተግባራትን አሟልቶ በማከናወን ረገድ የተጎዳ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱን የቤተሰብ መደበኛ አባል ስለአካለ ስንኩልነት ሁኔታ በመጠየቅ በዓምድ 28 ይመዘገባል፡፡

ሀ. ከዚህ በፊት በትምህርት ቤት የተማሩ ስለመሆናቸው ወይም

ለ. ፈጽሞ በትምህርት ቤት ገብተው ተምረው የማያውቁ ስለመሆናቸው ለቤተሰብ ኃላፊዎች ወይም ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ትክክለኛ መልስ ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎች በማቅረብና በማጣራት በትምህርት ላይ ላሉት ቀጥሎ ከተሰጠው ኮድ ዝርዝር በዓምድ 29 በካርድ ኮለም 53 እና 54 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል። ኮዱ የሚሞላው የተገኘውን መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በአጭሩ ከተጻፈ በኋላ ነው።

## የሚማሩበት ክፍል ደረጃ

ሀ. <u>በመማር ላይ ላሉ</u>

00 = ቅድመ ትምህርት ቤት ማለት በመለስተኛ ወይም ከአንደኛ ክፍል በታች ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

01 = በአንደኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

02 = በሁለተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

03 = በሦስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

04 = በአራተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

05 = በአምስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

06 = በስድስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

07 = በሰባተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

08 = በስምንተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

09 = በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

10 = በአሥረኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

11 = በአሥራ አንደኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

12 = በአሥራ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፤

20 = ከ12ኛ ክፍል በላይ በሆነ ት/ቤት ተቋም፤ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ዲግሪ /ቢ.ኤ፤ቢ.ኤስ.ሲ/ የሚያስገኝ ትምህርት በመከታተል ላይ ላሉ ሁሉ፤

21 = ከ12ኛ ክፍል በላይ በዩኒቨርሲቲ ወይም በኮሌጅ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ የሚያስገኝ ትምህርት በመከታተል ላይ ላሉ ሁሉ፣

22 = በዩኒቨርሲቲ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም በመማር ላይ ላሉ ሁሉ፣

23 = በመደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጎም በማይችል የት ምህርት መስክ ,ድርጅት ትምህርት በመከታተል ላይ ላሉ ለምሳሌ በቄስና በቁራን ትምህርት ቤት፣ በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሁሉ፣ አነስተኛ የትምህርት ዝግጅት የማይጠይቁ የማሠልጠኛ ተቋሞች፣

ለ. <u>ትምህርት ለተከታተሉና በቆጠራው ጊዜ በመማር ላይ ያልሆኑ፣</u>

24 = ከዚህ በፊት በትምህርት ቤት፣ ተቋም፣ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ለተከታተሉ ግን በቆጠራው ጊዜ በመማር ላይ ላልሆኑ ሁሉ፣

ሐ. <u>ትምህርት ተከታትለው ለማያውቁ፣</u>

25 = ከዚህ በፊት በማንኛውም ት/ቤት፣ተቋሞች፣...ወዘተ ትምህርት ተከ ታትለው ለማያውቁና በቆጠራው ጊዜም በመማር ላይ ላልሆኑ ሁሉ፣

አንዳንድ ሙሉ በሙሉ ቀጥታ በሆነ መንገድ መልስ ሊገኝላቸው የማይችሉ ሁኔታዎች ኖሩ ስለሚችሉ የሚከተለው ምሳሌ የመረጃ አሰባሰቡን ሁኔታ በይበልጥ ገልጽ ያደርገዋል፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የተገበረ ዕድ ትምህርት ቤት የአንደኛ ዓመት ምህርቱን አጠናቅቆ የሁለተኛ ዓመትን ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኝ የሚማርበት ክፍል ደረጃ ስንተኛ ነው? ይህ የሚገኘው ወደ ትምህርት ቤቱ ለመግባት በመደበኛ ምህርት ቤት ውስጥ ማጠናቀቅ ያለበት የክፍል ደረጃ አሁን ከደረሰበት የትምህርት መት በመደመር ይሆናል፡፡ ይኸውም ወደ ተገባረ ዕድ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚ ለው ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ትምህርት በማጠናቀቅ ስለሆነ አሁን የሚመርበት የክፍል ረጃ 12 /10+2/ መሆን አለበት፡፡

በመሠረተ ትምህርት በሚሰጣቸው ትምህርት ማንበብና መጻፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ያልቀጠሉ የሁለተኛ ክፍል ትምህርት እንዳ ጠናቀቁ ይቆጠራሉ፡፡

03 = የ3ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሁሉ

04 = የ4ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ

05 = የ5ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ

06 = የ6ኛ " " " "

07 = የ7ኛ " " " "

08 = የ8ኛ " " " "

09 = የ9ኛ " " " "

10 = የ10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ

11 = የ11ኛ " " " "

12 = የ12ኛ " " " "

20 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ ለማስገኘት ባልታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በሆነ ትምህርት ቤት፣ ተቋም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ፡፡

21 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ. ኤስ. ሲ/ ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲግሪ ያላገኙ ሁሉ፡፡

22 = የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ኤል.ኤል.ቢ/ያገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሁሉ፡፡

23 = በዩኒቨርሲቲ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም /ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ/ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን የኤም.ኤ፣ ኤም.ኤስ.ሲ ወይም ኤል.ኤል.ኤም ዲግሪ ያላገኙ ሁሉ፡፡

24 = የኤም.ኤ፣ የኤም.ኤስ.ሲ፣ ወይም የኤል.ኤል.ኤም /ማስተ የማስትሬት/ ዲግሪ ያገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሁሉ፡፡

25 = የዶክትሬት ዲግሪ ያገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ፡፡

05 = የተወሰነ ክፍያ የማያገኙ የቤት ውስጥ ሠራተኞች፣ እነዚህ ግለሰቦች የገንዘብ ወይም የዓይነት ክፍያ ሳያገኙ ማንኛውንም የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ የሚያከናውኑ እንደ ቤት እመቤት ዘመዶ፣ .....ወዘተ. ናቸው ።

06 = አካለ ስንኩል፣ እነዚህ ግለሰቦች በሰውነት ማጉደል ወይም በአእምሮ መታወክ ምክንያት ሥራ ለመሥራት ያልቻሉ ናቸው ። አካለ ስንኩል ሆነው በልመና ከተዳደሩ በለማኞች ይመደባሉ ።

07 = ለማኞች፣ እነዚህ ግለሰቦች በልመና የሚተዳደሩ ናቸው ። አካለ ስንኩል ሆነው ከሰመኑ እንደ ለማኞች ይቆጠራሉ ።

08 = ሴተኛ አዳሪዎች፣ በሴተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩ እንደ ቡና ቤት አሻሻጭ፣ መጠጥ ደርዳሪው ወይም ባይደረደሩ በዚህ ተግባር የሚተዳደሩና የመሳሰሉት ናቸው ።

09 = ልጅ፣ ዕድሜው ለሥራ ያልደረሰ በመሆኑ ያልሠራና በመማርም ያልሆነ ነው፣

10 = በጡረታ፣ በቤተሰብ እርዳታና መዋጮ የሚተዳደሩ፣ እነዚህ ግለሰቦች በቤት አበል፣ በጡረታ፣ እራሱ ባጠራቀመው ገንዘብ፣ በቤተሰብ እርዳታና መዋጮ የሚተዳደሩ ናቸው ። ያረጁ ተጧሪዎችም በዚህ ይመደባሉ ። ከላይ ከተጠቀሱት ሌሰ ከጋጠሙ በዚህ ይመደባሉ ።

ቀደም ብሎ የተጠቀሱትን የኮዶች ዝርዝር መሠረት በማድረግ የተገኘውን መልስ በዓምድ 33 በተሰጠው ቦታ በአጭር በመጻፍ በካርዱ ኮለሞች 59 እና 60 ኮዱ ይሞላል ።

ማሳሰቢያ፣

1. አንድ ግለሰብ ምንም እንኳን አካለ ስንኩል፣ አካለ ጉደሎ ወይም የአእምሮ በሽተኛ ቢሆንም በዓምድ 32 የተሰጠውን "የምርታማ ሥራን" ትርጉም የሚያሟላ ሥራ ከሠራ ሥራ እንደሠራ ይቆጠራል እንጂ ሥራ ያልሠራበት ምክንያት በኮድ "06" አካለ ስንኩል ተብሎ አይሞላለትም ።

- የቀነሾርቢቱ አስተማሪ
- ደራሲ
- ላይበረሪያን
- ልብስ ሠፊ
- ብረታ ብረት ሠራተኛ
- ጠላ ነጋዴ
- አናጢ
- መዝገብ ያዥ
- ታይፒስት
- ሹፌር
- የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ሠራተኛ
- የባንክ ቤት ገንዘብ ተቀባይ /ከፋይ/
- ፀሐፊ
- አራሽ ገበሬ /ሱሀል፣ቡና፣አትክል ፍራፍሬ፣ ጥጥ፣...ወዘተ/
- ከብት አርቢ /የሚያመርተትን ያጠቃልላል/
- እረኛ
- ዓሣ አጥማጅ
- ከሰል አከባይ

አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ የበለጠ ሥራ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በዓምድ 34 መመዝገብ ያለበት የሥራ ዓይነት ግለሰቡ ከሁለት ወይም ከሦስት ሥራ ዎች ውስጥ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ይበልጡን ጊዜ ያጠፋበት የሥራ ዓይነት ነው፡፡

በሚመለከተው ቤተሰብ ስም አንጻር የሥራው ዓይነት ይመዝገባል እንጂ ከ61–69 ባሉት ካርድ ኮለሞች ምንም አይሞላም፡፡

<u>ዓምድ 35 የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምንድን ነው?</u>

ዓምድ 35 ለመሙላት ግለሰቡ የት ወይም በየትኛው ድርጅት እንደሚሠራ በመጠየቅና ከዚያም ድርጅቱ ምን እንደሚያመርት፣ እንደሚነግድ /የጅምላ ወይም የችርቻሮ ንግድ/ ወይም ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዓምድ የምርቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የንግዱ ዓይነት ግልጽ በሆነ መንገድ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

ካለው እንደ ቤተሰቡ የሚኖርበት ቤት አካል በመውሰድ እንደ አንድ ክፍል ይቆጠራል፡፡ ቤተሰቡ ከሚኖርበት ቤት ወጭ የከብቶች ማደሪያ ቤት ካለ እንደ ቤት አይቆጠርም፡፡ ለቤቱ ቁጥርም አይሰጠውም፡፡፡

## ዓምድ 44፤ — የቤቱ የማድ ቤት ሁኔታ

በዚህ ዓምድ ውስጥ ቤቱ ለማድ ቤትነት ብቻ የሚያገለግል የተለየ ክፍል እንዳለው፣ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚያውሉትን ክፍል በተጨማሪ በማድቤትነት የሚገለገሉበት እንደ ሆነ ወይም ፈጽሞ ማድቤት እንደሌለው በመጠየቅ በዓምዱ እንደሁኔታው ይመዘገባል፡፡ ቤቱ ማድቤት የለውም ሲባል ለማድቤትነት ብቻ የተለየ ክፍል የሌለው ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚያውለውን ክፍል ለማድቤትነት ጭምር ሳይገለገል ሲቀርና ቤተሰቡ ከቤት ውጭ በሚገኝ በዛፍ ጥላ ሥር፤፤.... ወዘተ. ምግቡን ለማዘጋጀት የሚያገለግል ሲሆን ነው፡፡

ስለዚህ የቤቱ የማድቤት ሁኔታ በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የኮዶች ዓይነት በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ ከተደረገ በኋላ ይኸው ኮድ በዓምድ 42 በካርድ ኮለም 33 ይሞላል፡፡

1 = ማድቤት የለውም
2 = ለማድቤትነት ብቻ የሚያገለግል ክፍል አለው
3 = የሚያድሩበትን ቤት እንደማድቤት ይጠቀማሉ
4 = ከብቶች የሚያድሩበትን ቤት እንደማድቤት ይጠቀማሉ

## ዓምድ 45 ፡ — ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ውስጥ ከብቶች ያድራሉ?

ቤተሰቡ በሚያድርበት ቤት ከብቶች የሚያድሩ መሆናቸውን በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ በማድረግ ይኸውም ኮድ በዓምድ 43 በካርዱ ኮለም 34 ይሞላል፡፡

1 = ያድራሉ

2 = አያድሩም

## ክፍል 2 መሠረታዊ ሕዝብና ባሕሪያት ማጠቃለያ

ይህ ክፍል በቆጠራው ቦታ በለሚኖሩት ሰዎች ብዛት በጾታ፣ ባለፉት 12 ወራት በቤተሰቡ የተወለዱ ልጆች ብዛት፣ ባለፉት 12 ወራት ከቤተሰቡ በሞት የተለዩ አባላት ብዛት፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉና የሚችሉ ብዛት፣ እንዲሁም የብሔረሰብ ዓይነትና ብዛት የሚመዘገብበት ነው፡፡ ክፍል 2 መሞላት ያለበት በቅድሚያ የቆጠራው መጠይቆች በተሟላ ሁኔታ መሞላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

### ዓምድ 9 የቤት ተራ ቁጥር

በሕዝብና በቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 10 የቤት ተራ ቁጥር ተሞልቷል፡፡ ስለዚህ በቅጽ 4 ዓምድ 9 በካርድ ኮለም 18 — 20 ላይ ለሚመለከተው ቤተሰብ የሚሞላው ቁጥር በሕዝብና መኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 10 ? ተሞላው የቤት ተራ ቁጥር ነው፡፡

### ዓምድ 10 የነዋሪው ዓይነት

በሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 9 ካርድ ኮለም 23 የተሞላው የነዋሪ ዓይነት ኮድ በቅጽ 4 ዓምድ 10 ካርድ ኮለም 21 ላይ ይገለበጣል፡፡

### ዓምድ 11 የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር

በዓምድ 12 ለሚመዘገብ የነዋሪ ዓይነት ማለትም ለመደበኛ ቤተሰብ የቤተሰብ ኃላፊ ስም፣ ለሆቴልና ለሆስቴል ስም፣ መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች የሚያድሩበት ቦታ ስም በዚህ ዓምድ 001፣ 002፣ 003፣.... ወዘተ በማለት ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል፡፡

### ዓምድ 12 ስም

በዓምድ 10 በተጻፈው የነዋሪው ዓይነት ኮድና በዓምድ 11 በተጻፈው የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር አንጻር የተመለከተው መደበኛ ቤተሰብ ከሆነ የቤተሰብ ኃላፊ ስም፣ ሆቴልና ሆስቴል ከሆነ የሆቴሉና የሆስቴሉ ስም ሌላ ጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ከሆነ የጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ስም፣ እንዲሁም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ከሆነ የሚያድሩበት ቦታ ስም ይመዘገባል፡፡

ዓምድ 18 ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት፣

ቆጠራው በቆጠራው ቦታ ከተጠናቀቀ በኋላ በቆጠራው ቦታ ውስጥ የሚኖሩት ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት በቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ በዓምድ 18 በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ ብዛቱ የሚገኘው ከቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 16 ቢሆን ይኸም የመጨረሻውን የቤተሰብ ተራ ቁጥር በመውሰድ ይሆናል፡፡ በመመዝገቢያ ቅጽ የተገኘው የቤተሰቦች ብዛት በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ከተሞሉላቸው የቤተሰቦች ብዛት መሳከር አለበት፡፡ ካልተመሳከረ ግን የማጠቃለያው ቅጽ አሞላል ሁኔታ እንደገና በትክክል መፈጸሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 19 ጠቅላላ የመኖሪያ ቤቶችና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት

ቆጠራው በቆጠራ ቦታው ከተጠናቀቀ በኋላ በቆጠራ ቦታው ውስጥ ለመኖሪያ ብቻ እና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት፣ በቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ በዓምድ 19 በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ ብዛቱ የሚገኘው በቆጠራው ቦታ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ የተሞሉላቸውን መኖሪያ ቤቶች ብዛት በመቁጠር ይሆናል፡፡ ይህም የሚገኘው በቤት፣ በቤተሰብና በድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ–1 ከተመዘገቡት መደበኛ መኖሪያ ቤትና መደበኛ መኖሪያና ድርጅት /በቅጹ በዓምድ 12 ኮድ "1" እና ኮድ "2" የተሰጣቸው/ የሆኑ ቤቶች ብዛት ጋር መሳከር አለበት፡፡

ዓምድ 20 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ስም፣ ፊርማና ቀን

በመጨረሻም የቆጠራ የማጠቃለያ ቅጽ በትክክልና በተሟላ አኳኋን የተፈጸመ ስለመሆኑ ቆጣሪውና ተቆጣጣሪው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና ቀኑን ይሞላሉ፡፡

## ስለ ቆጠራ ቦታ ካርታ ዝርዝር መግለጫ

እያንዳንዱ ቆጣሪ ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪው አማካኝነት የተሠራ በበትን የቆጠራ ቦታ ካርታ እና ስለ ቆጠራው ቦታ የሚገልጽ የቆጠራ ቦታ መግለጫ ጽሑፍ ይደርሰዋል:: እያንዳንዱ ቆጣሪ እነዚህ ሁለቱ ከደረሱት በኋላ ስለ ተመደበበት የቆጠራ ቦታ በይበልጥ ለመረዳት ካርታውን ማጥናት ይኖርበታል::

### ሀ. በገጠር የሚገኝ የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙበታል

1. የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ፣ ወረዳ እና ገበሬ ማኀበር ስም፣
2. የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት የገበሬ ማኀበር ሊቀመንበር ስም፣
3. የቆጠራው ቦታ መለያ ቁጥር /ኮድ/
4. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ብዛት፣
5. የቆጠራው ቦታ ገምታዊ ስፋት፣
6. የቆጠራ ቦታ ድንበር ከትክክለኛ ስምና አቀማመጥ ጋር፣
7. በቆጠራ ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ መንደሮች ትክክለኛ አቀማመጥና ስማቸው፣
8. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ እና ድንበር አካባቢ የሚገኙ አንዳንድ ቤቶች፣ ወንዝ፣ የእርሻ ቦታ፣... ወዘተ
9. የቆጠራውን ቦታ የሚያቀስኑ ገበሬ ማኀበር ወይም ወረዳ ወይም ሌላ ቆጠራ ቦታ ስም፣
10. የቆጠራው ቦታ ሰሜናዊ አቅጣጫ፣
11. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ምልክቶች/ሌጀንድ/ በሥዕላዊ መልክ፣
12. የካርታው መስፈርት፣

### ለ. በከተማ የሚገኝ የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት አለበት

1. የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ እና ወረዳ፣
2. " " " የከተማ ስም፣
3. " " " ከፍተኛ እና ቀበሌ ቁጥር፣
4. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ የቤቶች እና የቤተሰቦች ብዛት፣
5. የቆጠራው ቦታ ገምታዊ ስፋት፣

ክፍለ ሀገር ........ ሸዋ

አውራጃ ............ ጨቦና ጉራጌ

ወረዳ ............. ኢሉ


የገበሬ ማህበር ስም .... አሰንን

የሊቀ መንበር ስም ...... አበባው አሰፋ

የቆጠራ ቦታ ቁጥር ..... 14—01

የቆጠራ ቦታ ስፋት ..... 8 ኪ.ሜ$^2$


የቤተሰብ ብዛት ......... 210




የቆጠራ ቦታ ቁጥር 14–02

መስፈርት 1:50,000

## መግለጫ



FORM R—5

Page 2 of 2 pages

# CENTRAL STATISTICAL OFFICE

## DESCRIPTION FORM FOR RURAL ENUMERATION AREA

1·REGION ሸዋ 2·AWRAJA ጨቦና፡ጉራጌ 3·WEREDA ኬ.ሶ.

4·EA· CODE № 14-01 5·NAME OF PAA/SUBDIVISION ከስንጉ

6·PAA/SUBDIVISION CODE № 14

### DESCRIPTION OF THE EA·


DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE THE CIRCUIT CLOCKWISE

የሚጀምረው፡ የእግር፡ መንገድ፡ ያድርጎና፡ ዲጋበማ፡ ገመዶን፡ ቤት
በሙሉና፡ የሚለ፡ ገደን፡ ቤት፡ በውሃ፡ በመደረግ፡ ከሰሰ፡ ቀበሌ፡
ወንዝ፡ ድረስ፡ ይቀበላል።

N.B. ATTACH THIS FORM TO FORM R-4 USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED

NAME OF G·A· [illegible] INITIAL [illegible] DATE 19/9/73


NAME OF SUPERVISOR [illegible] INITIAL [illegible] DATE 20/9/73



ክፍለ ሀገር----ሸዋ
ከተማ
01-01
01-01
መግለጫ
አስፋልት መንገድ
የበጋ መንገድ
ቤተ ክርስቲያን
ትምህርት ቤት
ቆርቆሮ ቤት
ሣር ቤት
ሆቴል

| | |
|---|---|
| ክ/ሀገር ሸዋ | ክፍተኛ 1 |
| አውራጃ የረርና ከረዩ | ቀበሌ 07 |
| ወረዳ አዳማ | የቀ/ሊ/መ/ስም ፊቃዱ ሀብቴ |
| ከተማ ናዝሬት | የቁ/ቦታ ቁ/ 1-07-01 |
| | የቤቶች ብዛት 155 |
| | የቤተሰብ ብዛት 130 |

ከላይ የተዘረዘሩት በፋይል ( ክላሴር ) በስተጀርባ ተጽፈው ይገኛሉ




## መግለጫ

- መንገድ
- የግቢ፡ ወሰን
- የቁጠሩ፡ቦታ፡ ክልል
- ቤት

1-07-01 የቁጠሩ፡ቦታ፡መ/ቁጥር

FORM U—4

Page __ of __ Pages

# CENTRAL STATISTICAL OFFICE

## FORM FOR DESCRIBING URBAN ENUMERATION AREA

1. REGION: ሸዋ
2. AWRAJA: የረርና ከረዩ
3. WEREDA: አዳማ
4. NAME OF URBAN CENTER: ናዝሬት
5. KEFETEGNA: 1
6. KEBELE: 07
7. E.A. №: 01

### DESCRIPTION OF THE E.A.

DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE THE DESCRIPTION CLOCKWISE

በሰሜን ፦ የባቡር ሐዲድ ወሰን ሆኖ ያገለግላል

በምሥራቅ ፥ የኢትዮጵያ ትቅደም ጎዳና ወሰን ሆኖ ያገለግላል

በደቡብ ፦ በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በቀበሌ 07 ጽ/ቤትና በመጋዘን 344 ፊትለፊት በሚገኘውና ሰፊ ግልጽ የመኪና መንገድ ይዋሰናል

እነዚህ የጠቀስኳቸው ጽ/ቤቶች ሁሉ በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው

ከቆጠራው ቦታ ክልል ውጪ የሚገኙት የከፍተኛ 1 ጽ/ቤትና መጋዘኑ ናቸው

በምዕራብ ፦ ወሉ አስፋልት በሆነው የምንጃር ጎዳና ይዋሰናል

NAME OF G.A.: ተሰማ ሁንደማ — INITIAL: [signature] — DATE: 8-4-74

NAME OF SUPERVISOR: መኮብብ — INITIAL: [signature] — DATE: 8-4-74


N.B. ATTACH THIS FORM TO FORM U-2 AND USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED

ክ/ሀገር ሸዋ
አውራጃ የረርና ከረዩ
ወረዳ አዳማ
ከተማ ናዝሬት

የመቆጣጠሪያ ቦታ ቁጥር 05
የቆጠራ ቦታ ብዛት 6

ከላይ የተዘረዘሩት በፋይል (ክላሴር) በስተጀርባ ተጽፈው ይገኛሉ

በከተማ የመቆጣጠሪያ ቦታ ምስል



| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሀረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1976 ዓ.ም. ያለፉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 54 | የገጠር መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 9 |
| 55 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 9 |
| 56 | የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአረፉበት | 1967 | 9 |
| 57 | የእናት አገር ጥሪ የተደረገበት | 1969 | 7 |
| 58 | የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ አንደኛ ጉባኤ የተካሄደበት | 1972 | 4 |
| 59 | የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. ሁለተኛ ጉባኤ የተካሄደበት | 1975 | 1 |

በኅ. ኢ.ት ጊ.ወ. መንግሥት
የሕዝብና የቤት ቆጠራ ኮሚሽን

# የ1976 ዓ.ም. የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ
# የቆጣሪዎች መመሪያ-ከተማ

አዲስ አበባ
የካቲት 1976 ዓ.ም.

## የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ አሞላል መመሪያ

### 1. የቅጹ አገልግሎት፣

ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ ለሚገኙት ቤቶች አገልግሎታቸውን፣ የድርጅቱ ዋና ምርት ወይም ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎትና የቋሚ ሠራተኞች ብዛት፣ የቤተሰብ ኃላፊና በግብርና ስለ ሚተዳደሩ የቤተሰብ አባላት መረጃዎች ለመመዝገብ ያገለግላል፡፡ ቅጹ በሁለት የተከፈለ ሲሆን ክፍል አንዱ የአካባቢ መለያ መመዝገቢያ ሆኖ ክፍል ሁለት የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ሁኔታ መመዝገቢያ ነው፡፡

### 2. የምዝገባው ዓላማ፣

የምዝገባው ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ በአገሪቱ ያሉትን ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶችን ብዛት ለማወቅ፣

ለ/ ቆጠራው በሚካሄድበት ወቅት ቤቶችና ቤተሰቦች እንዳይዘለሉና ተደጋግመው እንዳይቆጠሩ ለመቆጣጠር፣

ሐ/ የቤቶች የቤተሰቦችና የድርጅቶች ዝርዝር በማዘጋጀት ወደፊት ለሚከናወኑ የሶሻልና የኢኮኖሚ ጥናቶች የሚረዱ መረጃዎች ለማግኘት፡፡

### 3. የምዝገባው አፈጻጸም፣

በከተሞችና በገጠሩ የቤቶችና የመንገዶች አቀማመጥና አሠራር የተለያየ ነው፡፡ በከተሞች የቤቶች አቀማመጥ ለምዝገባው አመቺ እንደሆነ ሲገመት በገጠር የቤቶችና የመንገዶች አቀማመጥ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡

በከተማ የምዝገባው አፈጻጸም እንዴት መከናወን እንዳለበት ከዚህ ቀጥሎ ተገልጸአል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በከተሞች የቆጠራ ቦታ አንድና ከዚያ በላይ የሆኑ የተሸነሸኑ ዞኖች /ብሎኮች/ ይኖሩታል፡፡ ብሎክ አራቱም ማዕዘን ዙሪያውን በመንገድ፣ በክፍት ቦታ፣ በወንዝ ወይም በጫካ የተከበበ የከተማ አንድ ክፍል ነው፡፡

ከነዚህ ዞኖች /ብሎኮች/ አብዛኛውን ጊዜ ሥርዓት ባለው ሁኔታ በመንገድ እንደሚከፈሉ ይገመታል፡፡ ከዚህም በላይ በከተሞች ቤቶች የቀበሌ መለያ ቁጥር ተሰጥቶአቸዋል፡፡ የከተማ የቆጠራ ቦታ የሚያሳይ ምስል ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡ ምዝገባው በሚካሄድበት ወቅት የሚከተሉት ተግባራት መፈጸም አለባቸው፡፡

ሀ/ በመጀመሪያ የቆጠራ ቦታን ድንበር ዞር ማየትና ማጥናት፤

ለ/ የቆጠራ ቦታን በዞኖች /ብሎኮች/ መሸንሸን፤

ሐ/ ለተሸነሸኑት ዞኖች /ብሎኮች/ በቆጠራ ቦታው ካርታ ላይ ቁጥር መስጠት፤

መ/ በቆጠራው ቦታ ሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው ዞን /ብሎክ/ በመጀመር ወደ ምሥራቅ በመጓዝ እያንዳንዱ ቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት በቅደም ተከተል መመዝገብ፤


ሠ/ ምዝገባው የሚከናወነው በእያንዳንዱ ብሎክ የሚገኙትን ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መዝገብ ከጨረሱ በኋላ ወደሚቀጥለው ብሎክ በመሸጋገር ይሆናል፤

ረ/ ምዝገባው የተጀመረበትን ቦታ ለማመልከት በቆጠራው ካርታ ከመነሻው ላይ የ"×" ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል፤ ዋናው ቆጠራው በሚካሄድበትም ጊዜ በካርታው ላይ የ"×" ምልክት ከተደረገበት ቦታ መጀመር ያስፈልጋል፤


ሰ/ ምዝገባው በሚካሄድበት ጊዜ የመኪና መንገድን ብቻ መከተል ሳይሆን ወደ ቤትና ግቢ በስተጀርባ የሚያስኬዱትን የእግር መንገዶች በመጓዝ በቀራ ቤቶችን በሙሉ መመዝገብ ያስፈልጋል፤

ሸ/ የምዝገባው ሥራ ተጠናቀቀ የሚባለው በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙት ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች በሙሉ ሲመዘገቡ ነው፡፡

በገጠር የምዝገባው ሥራ አስቸጋሪ ስለማይሆን በከተማ ቆጠራ ቦታ የምዝገባ አፈጻጸም ሥርዓት በገጽ 10 በተሰጠው ምስል እንደተመለከተው ይሆናል፡፡




የቀበሌ ቦታ ካርታ — በከተማ




በከተማ ቆጠራ ቦታ የቤቶች፣ የቤተሰብና የድርጅት ምዝገባ አፈጻጸም ሥርዓት

## የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ቅጽ አሞላል መመሪያ፣

**ክፍል — 1 የአካባቢ መለያ**

ከዓምድ 1 — 8 ባሉት ዓምዶች የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት የአካባቢ መለያ መረጃ ይሞላል::

**ዓምድ—1 ክፍለ ሀገር**

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍትቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ስም ይመዘገባል::

**ዓምድ—2 አውራጃ**

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት አውራጃ ስም ይመዘገባል::

**ዓምድ—3 ወረዳ**

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ወረዳ ስም ይመዘገባል::

**ዓምድ—4 ከተማ**

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖረው በከተማ ከሆነ የከተማው ስም ይመዘገባል::

**ዓምድ—5 ከፍተኛ**

ቤተሰቡ የሚኖረው በከተማ ከሆነና ከተማውም ከፍተኛ ካለው በዚህ ዓምድ ከ9—10 ባሉት ካርድ ኮለሞች የከፍተኛው ቁጥር ይሞላል:: ቤተሰቡ የሚኖረው ከፍተኛ በሌለው ከተማ ከሆነ በዓምዱና በካርድ ኮለሙ የሠረዝ /—/ ምልክት ይደረጋል::

**ዓምድ—6 የመቆጣጠሪያ ቦታ**

ቤተሰቡ የሚኖርበት የመቆጣጠሪያ ቦታ ኮድ ቁጥር በዚህ ዓምድ ከ11—12 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል::

ዓምድ—10 <u>የቤት ቁጥር</u>

የቤት ቁጥር በዓምድ 10 ከመመዝገቡ በፊት የቤት፣ የመኖሪያ ቤትና የቤተሰብ ትርጉም ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

ሀ. <u>ቤት</u>

ቤት ማለት በአሠራሩ ተለይቶ "ራሱን የቻለ" ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ ወይም ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድርጅቱ ብቻ የሚያገለግል ነው።

<u>የቤቱ አሠራር የተለየ ነው</u>

የሚባለው ራያውን በግድግዳ፣ በአጥር ግቢ...ወዘተ የተከለለ ሆኖ ጣራውም በክዳን የተሸፈነ በመሆኑ በውስጥ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፣ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ለመለየት የሚያስችል ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በሳጠራ፣ በፕላስቲክ፣ በካርቶን፣...ወዘተ ግድግዳው የተሠራ ወይም በበና ጣራው በፕላስቲክ ክዳን የተሸፈነ ሆኖ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግል ቤት ሊያጋጥም ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንፃር ቢታይ ቤት ስለሆነ እንደቤት ይወሰዳል።

<u>የቤቱ አሠራር ራሱን የቻለ ነው</u> የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ ደረጃ፣ መሬት.... ወዘተ የራሱ መግቢያና መውጫ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተሳለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ሳይሆን በቀጥታ በራሳቸው ቤት መውጫ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው።

ለ. <u>መኖሪያ ቤት</u>

መኖሪያ ቤት ማለት ሙሉ በሙሉ ሰዎች የሚኖሩበት ወይም በከፊል እየኖሩ በቀረው ሌላ ተግባር ለምሳሌ ንግድ፣ ሽመና፣ የእንጨት ሥራ...ወዘተ የሚያከናውኑበት ቤት ማለት ነው። የመኖሪያ ቤት ለሰው መኖሪያ ተብሎ የተሠራ ወይም የተዘጋጀ ወይም ለመኖሪያ ተብሎ የተሠራ ወይም የተዘጋጀ ባይሆን በቆጠራው ጊዜ እንደ መኖሪያ የሚያገለግል ሊሆን ይችላል።

ዓምድ — 12 <u>የቤቱ አገልግሎት</u>

በዚህ ዓምድ ከዓምድ 9—11 የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል፡፡ የአገልግሎት ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ከዚህ ቀጥሎ ተዘርዝረዋል፡፡

1 = ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ
2 = ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት
3 = ለሆቴል
4 = ለሆስፒታል
5 = ለሌላ ጋር ዓሻ
6 = ለሌላ ድርጅት ብቻ
7 = ያልተያዘ
8 = በመሠራት ላይ ያለ

ከዚህ ቀጥሎ ለእያንዳንዱ የቤት አገልግሎት ዓይነት ትርጉምና የአመዘጋገቡ ሁኔታ ተብራርቷል፡፡

1. <u>ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የዋለ ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ መኖሪያ ብቻ" ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ የኮድ ቁጥር "1" በካርዱ ኮለም 28 ይሞላል፡፡

2. <u>ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ደግሞ ለድርጅት አገልግሎት የዋለ እንደሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለመደበኛ ቤተሰብ መኖሪያና ለድርጅት" ተብሎ ይመዘገብና ኮዱ "2" በካርዱ ኮለም 28 ይሞላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የድርጅት ትርጉም ተብራርቷል፡፡ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚለው ሆቴል፣ ሆስቴልና ሌላ ጋር ዓሻን አይጨምርም፡፡

## ድርጅት

ድርጅት ማለት በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ የቢሮ ወይም የኢኮኖሚ ተቋም ነው፡፡ ይኸውም የማምረቻ፣ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞችን ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ ዉሃ፣ ዓቦ፣ ጠርቃ ጠርቅ፣.... ወዘተ አምራቾችን፣ የዉሃ አደባት፣ የትራንስፖርት፣ የጤና፣ የትምህርት፣ የሕግ፣ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት እና ልዩ ልዩ ሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ የሚያከሄዱትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

ከላይ በተገለጠው የድርጅት ትርጉም መሠረት የቤት አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት የሚባለው በአንድ ቤት ውስጥ የቤተሰብ አባላት ከየኖሩበት አዚያው ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት የድርጅት ዓይነቶች ውስጥ አንዳን ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተግባራት ቢያከናውኑበት ነው፡፡ ይኸውም ለምሳሌ፡—

ቤት ለመኖሪያና ለመጠጥ መሸጫ /ጠላ፣ ጠጅ ሌሎች መጠጦች/
" " ለምግብ መሸጫ
" " ለሽመና
" " ለንግድ /ኪዮስክ/
" " ለሸክላ ሥራ
" " ለብረታ ብረት ሥራ
" " ለጫማ ሥራና ጥገና

በቤት ውስጥ የድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ባለቤቶች የሚኖሩበት ሲሆንና ነገር ግን ሠራተኞች የሚኖሩበት ከሆነ የቤት አገልግሎት ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት ተብሎ ይመዘገባል፡፡

## 3. ሆቴል

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለሆቴል ብቻ ከሆነ የቤት አገልግሎት ለሆቴል ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ በካርድ ከሰም 28 የኮድ ቁጥር 3 ይምሰል፡፡ በሆቴል ውስጥ በቤተሰብ መልክ የሚኖር እንደ ሆቴል ነዋሪ አንጂ እንደ ቤተሰብ አይቆጠርም ፡፡

ሆቴል፡— ማለት የምግብ፣ ወይም የመጠጥ ወይም የመኝታ አገልግሎት ወይ ንም ሁሉንም የሚሰጥ ድርጅት ነው ፡፡

4. <u>ሆስቴል</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ለሆስቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሆስቴል" ተብሎ በዓምድ 12 ተመዝግቦ በከርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር "4" ይሞላል።

ሆስቴል፦ ሆስቴል ማለት ብዙ ሰዎች ከመደበኛ ቤተሰብ አኗኗር ወጪ በአንድ ቤት ወይም ቤቶች በአንድነት እየኖሩ በቤቱም ያሉትን መገልገያዎች ማለት ውሃን፣ መብራትንና ሌሎች አገልግሎቶችን በጋራ ወይም በኅብረት የሚጠቀሙበትና በአንድ ድርጅት ሥር የሚተዳደሩበት የጋር ቆሽ መኖሪያ ሥፍራ ነው።

5. <u>ሌላ ጋር ቆሽ</u>

ሌላ ጋር ቆሽ የሚባሉት ከሆቴልና ከሆስቴል/በስተቀር ሌሎችን የጋር ቆሽ መኖሪያ ሥፍራዎችን በሙሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው።

ይኸውም፦ ወህኒ ቤቶች፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶች፣ ሕፃናት ማሳደጊያ፣ ሆስፒታሎች
የወታደር ካምፕ፣ ያረጁ ሰዎች መጦሪያዎች፣ /ገለስ ጠቢያ አሥር ቤት ካለ ነው/፣ የፀበል ማረሚያዎች፣ አድባራትና ገዳማት፣ የሠራተኛ ካምፖች፣.... ወዘተ ናቸው።

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከሆነ የቤት አገልግሎት "ሌላ ጋር ቆሽ" ተብሎ በዓምድ 12 ይመዝገብና በከርድ ኮለም 28 የኮድ ቁጥር 5 ይሞላል።

6. <u>ሌላ ድርጅት</u>

ሌላ ድርጅት የሚባሉት ሆቴልን፣ ሆስቴልንና "ሌላ የጋር ቆሽ" መኖሪያዎች ሳይጨምሩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የሚያጠቃልሉ ናቸው።

ይኸውም፦ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የማምረቻ ድርጅቶች፣ የንግድ ተቋሞች፣ ቤተ ክርስቲያኖችና መስጊዶች /የግለሰቦችን የጸሎት ቤቶች አይጨምርም/፣ መኝታ ቤት የሌለው ቡና ቤቶች፣ መኝታ ቤት የሌለው ገርበሬዎች፣ ጋራዥ፣ መጋዘን፣ ትምህርት ቤት፣.... ወዘተ

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን የሚሰጠው አገልግሎት ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ካልሆነ የቤቱ አገልግሎት "ሌላ ድርጅት" ተብሎ በዓምድ 12 ይመዘገብና በካርድ ክለም 28 የኮድ ቁጥር 6 ይምሰል።

7. <u>ያልተያዘ</u>

የተመዘገበው ቤት በቆጠራው ቀን በሆነ ምክንያት በአገልግሎት ላይ ያል ቀለ እንደሆነ "ያልተያዘ" ቤት ተብሎ በዓምድ 12 ይመዘገብና በካርድ ክለም 28 የኮድ ቁጥር 7 ይምሰል።

8. <u>በመሠራት ላይ ያሉ</u>

በመሠራት ላይ ያለ ቤት ማለት ቢያንስ ግድግዳው የቆመ ወይም ያለቀ ወይም ጣራው ያለቀ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ተሠርቶ ያልተጠናቀቀ ማለት ነው። የሚመዘገበው ቤት በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኝ ከሆነ "በመሠራት ላይ" ተብሎ በዓምድ 12 ይመዘገብና በካርድ ክለም 28 የኮድ ቁጥር 8 ይምሰል። ነገር ግን በመሠራት ላይ ያለ ቤት በቆጠራው ወቅት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የአገልግሎቱ ዓይነት በዓምዱ ይመዘገባል። ለምሳሌ በመሠራት ላይ ያለ ቤት ለመደበኛ መኖሪያ በማገልገል ላይ ካለ ለመደበኛ መኖሪያ ተብሎ ይመዘገባል። እንዲሁም ለድርጅት በማገልገል ላይ ካለ የድርጅቱን ዓይነት መመዝገብ ነው ። ይኸውም ሆቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት ለሆቴል፣ ለሆስቴል ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሆስቴል፣" ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ የቤቱ አገልግሎት "ለሌላ ድርጅት" ተብሎ ይመዘገባል።

ዓምድ 13—15 <u>ቤቱ ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሱቅ ጋርዥ ወይም ለሌላ ድርጅት ከሆነ</u>

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት ቤቱ በቆጠራው ቀን ለመደበኛ መኖሪያና ለድርጅት፣ ለሆቴል፣ ለሆስቴል፣ ለሱቅ ጋርዥ ወይም ለሌላ ድርጅት የሚያገለግል ከሆነ ነው።

2 = ከብት እርባታ ብቻ /ምንም ሰብል ሳያመርት ከብት ብቻ የሚያረቡ/

3 = ሌላ ግብርና /ዶሮ እርባታ፣ ንብ እርባታ፣ ዓሣ ማስገር፣ ከሰል ማክሰል፣... ወዘተ /

4 = ሰብልና ከብት እርባታ /ሰብል እያመረተ አንዱ ከብት ወይም ከዚያ በላይ የሚያረቡ/

5 = ሰብልና ሌላ ግብርና

6 = ከብት እርባታና ሌላ ግብርና

7 = ሰብል፣ ከብት እርባታና ሌላ ግብርና

ዓምድ — 19 <u>አስተያየት</u>

ይህ ዓምድ መዝገበው በሚካሄድበት ወቅት ከመዝገበው ጋር ግንኙነት ያላቸው ችግሮች/ሌሎች ሁኔታዎች ያጋጠሙ እንደሆነ ይመዘገብበታል፡፡

## 1976 የኢትዮጵያ የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች

## ቆጠራ መጠይቅ አሞላል መመሪያ

## ማሟያ

<u>ለሆቴልና ለሆስቴል ነዋሪዎች፣ ለሌላ ጋርዮሽ ነዋሪዎች እንዲሁም ቤት ለሌላቸው ግለሰቦች እንደ መደበኛ ቤተሰብ አባላት የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች መጠይቅ ይሞላላቸዋል፡፡ መጠይቆቹ በሚሞሉበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች በጥንቃቄ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡</u>

ሀ. <u>የሆቴል፣ የሆስቴልና የሌላ ጋርዮሽ ነዋሪዎችን በሚመለከት</u>

በዓምድ 9 የነዋሪው ዓይነት በሚመለከት የሆቴልና የሆስቴል ወይም ሌላ ጋርዮሽ ነዋሪ ለሚለው የተሰጠው መልስ ኮድ በካርድ ኮለም 23 ውስጥ ለተሞላላቸው በሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ውስጥ የሚከተሉት ዓምዶች ወይም ክፍሎች አይሞሉም፡፡ ማንኛውም በሆቴሉ ወይም በሆቴሉ አጥር ግቢ በቤተሰብ ወይም በሆቴል የአንድነት ስርዓት የሚኖር እንደሆኑ ነዋሪ ተወስዶ መጠይቁን ይሞላለታል ፡፡

መጠይቁ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የየክፍሉም አሞላል መመሪያ ከዚህ በታች ተመልክቷል።

## ክፍል አንድ — የአካባቢ መለያ

ከዓምድ 1—13 ባሉት ዓምዶች የቆጠረው ክልል የሚገኝበት የአካባቢ መለያ መረጃ ይሞላል።

### ዓምድ 1 — ክፍለ ሀገር

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ክፍለ ሀገር ስም ይመዘገባል።

### ዓምድ 2 — አውራጃ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት አውራጃ ስም ይመዘገባል።

### ዓምድ 3 — ወረዳ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ቤተሰቡ የሚኖርበት ወረዳ ስም ይመዘገባል።

### ዓምድ 4 — ከተማ

በዓምድ 4 በተሰጠው ክፍት ቦታ የከተማው ስም ይመዘገባል።

### ዓምድ 5 — ከፍተኛ

ቤተሰቡ የሚኖረው ከፍተኛ ባለው ከተማ ከሆነ በዚህ ዓምድ በካርዱ ኮለም 14—15 የከፍተኛ ቁጥር ይሞላል። ቤተሰቡ የሚኖረው ከፍተኛ በሌለው ከተማ ከሆነ በዚህ ዓምድ የሠረዝ /—/ ምልክት ይሞላል።

### ዓምድ 6 — የመቆጣጠሪያ ቦታ

ቤተሰቡ የሚኖርበት የመቆጣጠሪያ ቦታ ኮድ በዓምድ 6 ከ16—17 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል።

ዓምድ 7 — ቀበሌ ማኅበር

ቤተሰቡ የሚኖርበት የቀበሌ ማኅበር ኮድ በዓምድ 7 ከ18–20 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል።

ዓምድ 8 — የቆጠራ ቦታ

ቤተሰቡ የሚኖርበት የቆጠራ ቦታ ኮድ በዓምድ 8 ከ21–22 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይሞላል።

ዓምድ 9 — የነዋሪ ዓይነት

የነዋሪ ዓይነት መደበኛ ቤተሰብ፣ የሆቴልና የሆስቴል፣ ሌላ የጋርዮሽ ቤት ነዋሪ ወይም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ግለሰቦች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ መጠይቁ የሚሞላለት ቤተሰብ ወይም ግለሰብ የነዋሪውን ዓይነት በመለየት ከሚከተሉት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በካርድ ኮለም 23 ይሞላል።

1 = መደበኛ
2 = ሆቴልና ሆስቴል ነዋሪ
3 = ሌላ የጋርዮሽ ነዋሪ
4 = ቤት የሌላቸው

ዓምድ 10 — የቤት ተራ ቁጥር

በቤት፣ በቤተሰብና በድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ 1 በዓምድ 9 በምዝገባው ወቅት የቤት ተራ ቁጥር ተሞልቷል። በቅጽ 1 በዓምድ 9 የተመለከተውን የቤት ተራ ቁጥር በዓምድ 10 ከ24–26 ባሉት ካርድ ኮለሞች መገልበጥ ያስፈልጋል።

ዓምድ 11— የቤት ቁጥር

በዓምድ 11 የሚሞላው የቤት ቁጥር በቤቶች፣ በቤተሰቦችና፣ በድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ በዓምድ 10 የተመዘገበውን የቤት ቁጥር በመገልበጥ ነው። ቤቱ የቤት ቁጥር ከሌለው ዓምዱ ሠረዝ " — " ይሞላል።

አንግዶችን በሚመለከት በተለይ መገንዘብ የሚያስፈልገው ስለ አንግዶች የሚ ጠየቁት የመረጃዎች ዓይነት ስም፣ የነዋሪ ሁኔታ፣ ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለ ዝም ድና፣ ጾታና ዕድሜ ብቻ ናቸው። እነዚህም ከዓምድ 15—19 ያሉትን ይመለከታል።

## ዓምድ 15.1 — ማስታወሻ

በዓምድ 15 የተመዘገቡትን መደበኛ የቤተሰብ አባላትና የአንግዶች ሙሉ ስም ለመልስ ሰጪው ማንበብና የተመዘገቡትን ብዛት በመንገር ሳይመዘገብ የቀረ መደበኛ አባል ወይም እንግዳ ካለ በዓምድ 15 መመዝገብ ያስፈልጋል።

## ዓምድ 16 — የነዋሪ ሁኔታ

የነዋሪ ሁኔታ ሦስት ሲሆን ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፡—

1 = በእለቱ ቤት የነበረ ነዋሪ፡— የሚባለው መደበኛ የቤተሰቡ አባል ሆኖ ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቤት የነበረ ናቸው።

2 = በእለቱ ቤት ያልነበረ ነዋሪ፡— የቤተሰቡ መደበኛ አባል ሆኖ ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቤት ያልነበረ ናቸው።

3 = በእለቱ ቤት ያደረ እንግዳ፡— የቤተሰቡ መደበኛ አባል ባይሆን ቆጠራው በተካሄደበት እለት ቆጠራው በሚካሄድበት ቤት ያደረ ግለሰብ ናቸው።

ስለዚህ ከላይ በተሰጠው ትርጉም መሠረት የሚከተሉትን ኮዶች በመጠቀም በዓምድ 16 በካርድ ኮለም 32 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል።

1 = ቤት የነበረ ነዋሪ
2 = ቤት ያልነበረ ነዋሪ
3 = ቤት ያደረ እንግዳ

## ዓምድ 17 — ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና

በዓምድ 15 የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሚመዘገቡበት ጊዜ በመጀመሪያው መስመር የሚመዘገበው ሁልጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ ይሆናል። ስለዚህ በዓምድ 17 በመጀመሪያው መስመር "ኃላፊ" ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ እያንዳንዱ የቤተሰብ መደበኛ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና በተሰጠው ክፍት ቦታ ተጽፎ ይሞላል። ለምሳሌ

**ኮድ** **ብሔረሰብ**

08.... ቀገ
09.... ቅማንት
10.... ቤኝ፣ በዓዊ፣ ሀዓረብ
11.... ኦሮሞ /ቱለማ፣ ኢቱ፣ ከረዩ፣ ወሎ፣ ለሙ፣ ሊቃ፣ ገለን፣
በቾ፣ አበቹ፣ ሰላሌ፣ አርሲ፣ አራያ አዘቦ/
12.... ቦረና
13.... ጉጂ
14.... አርቦሬ፣ ኢርቦሬ፣ አልጌ
15.... ቡኪ፣ ሞቢያ
16.... ዳሰነች፣ ገለብ፣ ገለባ
17.... ገቀዳ፣ ማሽሌ፣ ኮሎ /ጎበዜ፣ ወርዜ፣ አሌ/
18.... ጊዶሌ፣ ዳራሼት፣ ጋርዳሰ፣ ዲራይታት፣ ዳራቴ
19.... ኮንሶ /ካራቴ/
20.... ፀማይ፣ በማይ /ዱሜ፣ ኩዌሎ/
21.... ሲዳማ
22.... ቡርጂ ዳሺ፣ በምበሳ
23.... ጌዴኦ፣ ደራሳ
24.... ሀዲያ፣ አዲያ
25.... ከምባታ፣ [illegible] ሀደሀያ
26.35... [illegible] ጋንዛ ሲሶ፣ ሺዶ [illegible] ገበሬ
27.36... [illegible]
28.... ቀቤና
29.... አፋር፣ ዳናኪል፣ ዳንካሊ /በለውሲ፣ ዓሞሀታ
ዳሂሚስ፣ አንከሳ፣ ሞዳይቶ/
30.... ቦሜሌ/ ዳርዶ፣ አቡቆ፣ ሀውያ፣ ገዶቡርሲ፣ አቡ/
31.... ባሆ፣ ሸሆ /ደበሬ ሜላ፣ ዓሳውርታ፣ ሚኒፈሬ፣ ሀንሀዚ፣
አርባ፣ ጠረውክ/
32.... ሜስ፣ /ሰንፋሎ፣ ጋንዛ፣ ሲንዳ፣ ገሞ፣ ሰሃቤ፣ ዳኒር/
33.... አፊ፣ አሬ፣ አር /ቢኮ፣ ሽንጋሜ፣ ካሎ/
34.... ሀመር፣ በሻዳ /ቤና፣ ካሮ/
35.... ዳሜ
36.... ዲዜ፣ ሜጂ

| ክዶ | ብሔረሰብ |
|---|---|
| 37.... | የሙባ፣ የማ፣ ዳንጀር |
| 38.... | ቤንች፣ ቤንችናን፣ ሼ፣ ጊሚራ |
| 39.... | ከፋ፣ ከፋቾ /ጎንጋ፣ ቦሻጋር/ |
| 40.... | ናኦ፣ ናዎ |
| 41.... | ሞቻ፣ ሼኮ |
| 42.... | ሻኮ፣ ዲዚ፣ ሡሳ፣ ደርባ፣ ደርቦ፣ ደርበ |
| 43.... | ሽናሻ፣ ቦሮ /ዓርጆ፣ ሹኮ፣ ሰሜን ሹኮ/ |
| 44.... | ደሜቴ፣ ኩሎ፣ ዳውሮ |
| 45.... | ኮንታ |
| 46.... | ባስኬቶ፣ አንጋሳ፣ ማሸራ /ደኮ፣ ደሎ ደሳ/ |
| 47.... | ደርዜ |
| 48.... | ጋሞ |
| 49.... | ጋንጁሌ፣ ባጫ |
| 50.... | ጎፋ፣ ገኑ |
| 51.... | ቁጨም፣ ቋጨም፣ ጋጸም፣ ሀፋር |
| 52.... | ኮይራ፣ አማሮ፣ አመርቴ፣ ጊዲቾ |
| 53.... | ማሌ |
| 54.... | ማሎ፣ ዓውሳ |
| 55.... | ጨራ |
| 56.... | ወላይታ |
| 57.... | ዘይሴ፣ ዘርጉላ |
| 58.... | አይዳ |
| 59.... | ሱርማ፣ ቲርማ፣ ዓማ |
| 60.... | ጓጉ፣ ቢጉ፣ ሙጉጂ፣ ቁጂ፣ ኛዪ ኒ |
| 61.... | መኤን፣ መቀን፣ ዓይና፣ ባርኮሞ /ቦዲ፣ ቦዲ፣ ተሽና፣ ሚኒት/ |
| 62.... | መበንጎ፣ ማጃንግ፣ መዘንገር |
| 63.... | ሙርሲ፣ ሙጉ፣ ሙኒ፣ ኰሳበንግ፣ ጣማ |
| 64.... | ቡሬ፣ ቻይ፣ ኾርማ |
| 65.... | ዘልማም፣ ባሌ፣ ማሌ፣ ዓሪማም |
| 66.... | ሙርሌ /ኩሰዎ ሙርሌ፣ አም ሙርሌ፣ ሌሎች/ |
| 67.... | አኙዋ፣ አኙዋክ፣ የሙብ |
| 68.... | ማባን |

| ኮዱ | ብሔረሰብ |
|---|---|
| 69.... | ትቁር፣ አቢጋር |
| 70.... | ኛንጋቶም፣ ቱርካና፣ ቡሜ |
| 71.... | በርታ |
| 72.... | ጋሚሊ |
| 73.... | ጎበቶ |
| 74.... | ሚቶ |
| 75.... | ነዓሺ |
| 76.... | ፊኩንኩም |
| 77.... | ኩንፋ |
| 78.... | ገባቶ |
| 79.... | ቤኒሻንጉል |
| 80.... | ጀበላዊ፣ አርቦ |
| 81.... | ኩናማ፣ በዓ፣ ከዛን፣ ባዛ /ኮማይሽ በርከ፣ ቢታማ፣ ኢሉትኝ ማርዓ፣ በቲት፣ በኅዓስ፣ ዕካ/ |
| 82.... | ወይጦ |
| 83.... | ፊሰሺ፤ ካይላ፣ ቤተስራኤል |
| 84.... | ከማ፣ ከሞ፣ ሀያሀያ፣ መዐን |
| 85.... | ቤ ሕቁር ኛንገዛ፣ ጋንዛ /ሲበ፣ ሸይ ሾኩሁ፣ ገበጨሬና |
| 86.... | ~~[illegible]~~ |
| 87.... | ሸታ፣ ሼታ፣ ሰንጋ |
| 88.... | ናሬ፣ በሬያ፣ ማርዓ /ሂገር፣ ቀጋሬብ በንቶሬ፣ ኮይታ፣ ኮይቻ/ |
| 95.... | ብሔረሰባቸው ያልታወቀ ኢትዮጵያውያኖች |
| 96.... | ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ሰዎች |
| 97.... | ከተሰጁ ብሔረሰቦች የተወለዱ |
| 98.... | ሌሎች ብሔረሰቦች |

x = ከልደት ጀምረው ያለማቋረጥ እስከ ቆጠራው ቀን ድረስ በከተማው ለሚኖሩና አዲስ ለተወለዱ ሕፃናት፡፡

0 = ከዓመት በታች ያለማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

1 = አንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በታች ያለ ማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

2 = ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከሦስት ዓመት በታች ያለ ማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

3 = ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከአራት ዓመት በታች ያለ ማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

4 = አራት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከአምስት ዓመት በታች ያለ ማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

5 = አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ነገር ግን ከስድስት ዓመት በታች ያለማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

6 = ከስድስት እስከ 9 ዓመት ያለማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

7 = ከአሥር እስከ 15 ዓመት ያለማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

8 = ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ያለማቋረጥ በከተማው ለኖሩ፣

## ዓምድ 28 የአካል ስንኩልነት ሁኔታ፣.... ልበስ ስንኩል ናቸው? ከሆኑ ዓይነቱ ይገለጽ

ሲወለዱ ወይም ከተወለደ በኋላ የሰውነት፣ የአእምሮ፣ ወይም የሌላ የአካል ክፍል መበላሸት የደረሰበት ግለሰብ አካለ ስንኩል ይባላል፡፡ በአጠቃላይ አካለ ስንኩል የሚባለው ግለሰቡ የአካሉ ክፍል በመሰናከሉ፣ በመጉዳቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት ሌሎች ደህና የሆኑ ሊያከናውኑት የሚችሉትን ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን ባለመቻሉ የበሽልና የኢኮኖሚ ተግባራትን አሟልቶ በማከናወን ረገድ የተጓጎለ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱን የቤተሰብ መደበኛ አባል ስለአካለ ስንኩልነት ሁኔታ በመጠየቅ በዓምድ 28 ይመዘገባል፡፡

ሀ. ከዚህ በፊት በትምህርት ቤት የተማሩ ስለሆናቸው ወይም

ለ. ፈጽሞ በትምህርት ቤት ገብተው ተምረው የማያውቁ ስለሆናቸው ለቤተሰብ ኃላፊዎች ወይም ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ትክክለኛ መልስ ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎች በማቅረብና በማጣራት በትምህርት ላይ ላሉት ቀጥሎ ከተሰጠው ኮድ ዝርዝር በዓምድ 29 በካርድ ኮለም 53 እና 54 ትክክለኛው ኮድ ይሞላል፡፡ ኮዱም የሚሞላው የተገኘውን መልስ በተሰጠው ክፍት ቦታ በእጥሩ ከተጻፈ በኋላ ነው፡፡

## የሚማሩበት ክፍል ደረጃ

ሀ. **በመማር ላይ ያሉ**

00 = ቅድመ ትምህርት፣ቄስ ማስተ፣መሰማመሻ ወይም ከአንደኛ ክፍል በታች ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

01 = በአንደኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

02 = በሁለተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

03 = በሦስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

04 = በአራተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

05 = በአምስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

06 = በስድስተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

07 = በሰባተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

08 = በስምንተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

09 = በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

10 = በአሥረኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

11 = በአሥራ አንደኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

12 = በአሥራ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ በመማር ላይ ያሉ ሁሉ፣

20 = ከ12ኛ ክፍል በላይ በሆነ ት/ቤት ተቋም፣ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ቢ.ኤስ.ሲ/ የሚያስገኝ ትምህርት በመከታተል ላይ ያሉ ሁሉ፣

21 = ከ12ኛ ክፍል በላይ በቴክኒክ ወይም በኮሌጅ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ የሚያስገኝ ትምህርት በመከታተል ላይ ላሉ ሁሉ፣

22 = በቴክኒክ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም በማመር ላይ ላሉ ሁሉ፣

23 = በመደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጎም በማይችል የትምህርት መስጫ ድርጅት ትምህርት በመከታተል ላይ ላሉ ለምሳሌ በቄስና በቀራን ትምህርት ቤት፣ በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሁሉ፣ አነስተኛ የትምህርት ዝግጅት የማይጠይቁ የማሠልጠኛ ተቋሞች፣

ለ. <u>ትምህርት ለተከታተሉና በቆጠራው ጊዜ በመማር ላይ ያልሆኑ፣</u>

24 = ከዚህ በፊት በትምህርት ቤት፣ ተቋም፣ ኮሌጅ ወይም ቴክኒክ ትምህርት ለተከታተሉ ነገ በቆጠራው ጊዜ በመማር ላይ ላልሆኑ ሁሉ፣

ሐ. <u>ትምህርት ተከታትለው ለማያውቁ፣</u>

25 = ከዚህ በፊት በማንኛውም ት/ቤት፣ ተቋም፣...ወዘተ ትምህርት ተከታትለው ለማያውቁና በቆጠራው ጊዜም በመማር ላይ ላልሆኑ ሁሉ፣

አንዳንድ ሙሉ በሙሉ ቀጥታ በሆነ መንገድ መልስ ሊገኝላቸው የማይችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የሚከተለው ምሳሌ የመረጃ አሰባሰቡን ሁኔታ በይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል::

በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኘው የተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት የአንደኛ ዓመት ትምህርቱን አጠናቆ የሁለተኛ ዓመቱን ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኝ የሚማርበት የክፍል ደረጃ ስንተኛ ነው? ይህ የሚገኘው ወደ ትምህርት ቤቱ ለመግባት በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ማጠናቀቅ ያለበት የክፍል ደረጃ አሁን ከደረሰበት የትምህርት ዓመት በመደመር ይሆናል:: ይኸውም ወደ ተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ለመግባት የሚቻለው ቢያንስ የ10ኛ ክፍል ትምህርት በማጠናቀቅ ስለሆነ አሁን የሚማርበት የክፍል ደረጃ 12 /10+2 / መሆን አለበት::

በመሠረተ ትምህርት በሚሰጠው ትምህርት ማንበብና መጻፍ ችለው
በሌላ ቦታ ትምህርት ያልቀጠሉ የሁለተኛ ክፍል ትምህርት እንዳ
ጠናቀቁ ይቆጠራሉ።

03 = የ3ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁና ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ሁሉ

04 = የ4ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ

05 = የ5ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ

06 = የ6ኛ " " " "

07 = የ7ኛ " " " "

08 = የ8ኛ " " " "

09 = የ9ኛ " " " "

10 = የ10ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ

11 = የ11ኛ " " " "

12 = የ12ኛ " " " "

20 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ ለማስገኘት ባልታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በሆነ ትምህርት ቤት፣ ተቋም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ።

21 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ /የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲግሪ ያላገኙ ሁሉ።

22 = የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ኤል.ኤል.ቢ/ ያገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሁሉ።

23 = በዩኒቨርሲቲ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም /ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ/ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን የኤም.ኤ፣ ኤም.ኤስ.ሲ ወይም ኤል.ኤል.ኤም ዲግሪ ያላገኙ ሁሉ።

24 = የኤም.ኤ፣ የኤም.ኤስ.ሲ፣ ወይም የኤል.ኤል.ኤም /ማለት የማስትሬት/ ዲግሪ ያገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሁሉ።

25 = የዶክትሬት ዲግሪ ያገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ።

06 = <u>የተወሰነ ክፍያ የማያገኙ የቤት ውስጥ ሠራተኞች፡</u> እነዚህ ግለሰቦች የገንዘብ ወይም የዓይነት ክፍያ ባያገኙ ማንኛውንም የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ የሚያከናውኑ እንደ ቤት እመቤት ዘመድ፣... ወዘተ ናቸው፡፡

07 = <u>አካለ ስንኩል፣</u> እነዚህ ግለሰቦች በሰውነት መጉደል ወይም በአእምሮ መታወክ ምክንያት ሥራ ለመሥራት ያልቻሉ ናቸው፡፡ አካለ ስንኩል ሆነው በልመና ከተዳደሩ በለማኞች ይመደባሉ፡፡

08 = <u>ለማኞች፣</u> እነዚህ ግለሰቦች በልመና የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ አካለ ስንኩል ሆነው ከለመኑ እንደ ለማኞች ይቆጠራሉ፡፡

09 = <u>ቤተኛ አዳሪዎች፣</u> በቤተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩ እንደ ቡና ቤት አሻሻጭ፣ መጠጥ ያርድረው ወይም ሳይያረድሩ በዚህ ተግባር የሚተዳደሩና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

10 = <u>ልጅ፣</u> ዕድሜው ለሥራ ያልደረሰ በመሆኑ አንዱም ቀን ያልሠራ ነው፡፡

11 = <u>በጡረታ፣ በቤተሰብ አርዳታና መዋጮ የሚተዳደሩ፣</u> እነዚህ ግለሰቦች በቤት አበል፣ በጡረታ፣ አራሱ ባጠራቀመው ገንዘብ፣ በቤተሰብ አርዳታና መዋጮ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ያረጁ ተጧሪዎችም በዚህ ይመደባሉ፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሌላ ካጋጠመም በዚህ ይመደባሉ፡፡

ቀደም ብሎ የተጠቀሱትን የኮዶች ዝርዝር መሠረት በማድረግ የተገኘውን መልስ በዓምድ 33 በተሰጠው ቦታ በመጻፍ በካርድ ኮሎኖች 59 እና 60 ኮድ ይሞላል፡፡

<u>ማሳሰቢያ፣</u>

1. አንድ ግለሰብ ምንም እንኳን አካለ ስንኩል፣ አካለ ጉደሎ ወይም የአእምሮ በሽተኛ ቢሆንም በዓምድ 32 የተሰጠውን "የምርታማ ሥራን" ትርጉም የሚያሟላ ሥራ ከሠራ ሥራ እንደሠራ ይቆጠራል እንጂ ሥራ ያልሠራበት ምክንያት በኮድ "06" አካለ ስንኩል ተብሎ አይሞላለትም፡፡

- የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ
- ደራሲ
- ላይብረሪያን
- ልብስ ሠፊ
- ብረታ ብረት ሠራተኛ
- ጠላ ነጋዴ
- አናጢ
- መዝገብ ያዥ
- ታይፒስት
- ሹፌር
- የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ሠራተኛ
- የባንክ ቤት ገንዘብ ተቀባይ /ከፋይ/
- ፀሐፊ
- አራሽ ገበሬ/ሰብል፣ቡና፣አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ጥጥ፣...ወዘተ/
- ከብት አርቢ/የሚያመርቶትን ያጠቃልል/
- አረኛ
- ዓሣ አጥማጅ
- ከሰል አከባይ

አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ የበለጠ ሥራ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በዓምድ 34 መመዝገብ ያለበት የሥራ ዓይነት ግለሰቡ ከሁለቱ ወይም ከሦስቱ ሥራዎች ውስጥ ባለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ይበልጡን ጊዜ ያጠፋበት የሥራ ዓይነት ነው፡፡

በሚመለከተው ቤተሰብ ሰው አንጻር የሥራው ዓይነት ይመዝገባል እንጂ ከ61—63 ባሉት ካርድ ኮለሞች ምንም አይሞላም፡፡

<u>ዓምድ 35 የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምንድን ነው?</u>

ዓምድ 35 ለመሙላት ግለሰቡ የት ወይም በየትኛው ድርጅት እንደሚሠራ በመጠየቅና ከዚያም ድርጅቱ ምን እንደሚያመርት፣ እንደሚነግድ /የጅምላ ወይም የችርቻሮ ንግድ/ ወይም ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ዓምድ የምርቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የንግዱ ዓይነት ግልጽ በሆነ መንገድ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

፯. ስለ ቤት መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት በተለይም የቤቱ ግድግዳ፣ ጣራ፣ ወለልና ክርኒስ የተሠራበት ዕቃ ዓይነት በሚመለከት የዕቃውን ዓይነት በጥንቃቄ አጣርቶ ትክክለኛውን መልስ መመዝገብ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም መልስ ሰጪውን ለመርዳት በቤቱ ተዘዋውሮና የቤቱን ክፍሎች በሥርዓት ተመልክቶ ትክክለኛውን መልስ በተገቢው ዓምዶች መመዝገብ ያስፈልጋል::

፰. ቤትን በሚመለከት የተሰጡትን ትርጉሞች እንደ ክፍል፣ ጣራ፣ ክርኒስ፣ ዘመናዊ ማድ ቤት፣ ዘመናዊ ያልሆነ ማድ ቤት፣ የተጠበቀ ውሃ፣... ወዘተ በሚገባ በመረዳትና ለመልስ ሰጪው በማብራራት ትክክለኛውን መልስ ማግኘትና በሚመለከተው ዓምድ መመዝገብ ያስፈልጋል::

<u>ዓምድ 42 የቤቱ ዓይነት ምንድን ነው ?</u>

የቤቱ ዓይነት ሲባል የሚከተሉትን ያጠቃልላል::

1 = ቋሚ  3 = ተንቀሳቃሽ
2 = ጊዜያዊ  4 = ሌላ /ይገለጽ/_____

<u>ቋሚ ቤት፣</u>

ቋሚ ቤት ማለት ቤቱ ለብዙ ዓመታት አገልግሎት ለመስጠት የሚችል ሆኖ ከድንጋይ፣ ከሸክላ፣ ከብሎኬት፣ ከሲሚንቶ ወይም ሌሎች ከአካባቢው ከተገኙ የሕንፃ መሥሪያዎች የተሠሩትን ቤቶች ያጠቃልላል:: ለምሳሌ ቪላ፣ ፎቅ፣ የጭቃ ቤቶች፣... ወዘተ በዚህ ሥር ይመደባሉ::

<u>ጊዜያዊ ቤት፣</u>

ጊዜያዊ ቤት ማለት ጊዜያዊ መጠለያ እንዲሆኑ የተሠሩ መኖሪያ ቤቶችን ያጠቃልላል:: አሠራራቸውም እንጨት በመሬት በመትከል ቋሚነት በሌለው ግድግዳ እንዲሁም በካርቶን፣ በቆርቆሮ ከዳን፣... ወዘተ የተሠራ ሲሆን በተወሰነ ጊዜ ሰዎች የሚኖሩበት ነው:: ለምሳሌ ዳስ በተወሰነው ጊዜ ሰው እስከኖረበት እንደ ጊዜያዊ ቤት ሊቆጠር ይችላል::

አብዛኛው የቤቱ ጣራ የተሠራበትን የሕንፃ ዕቃ ዓይነት በመጠየቅና በተሰጠው መልስ ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝሮች ውስጥ በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በካርድ ኮሎም 34 ውስጥ ይሞላል፡፡ ከተዘረዘረው ኮድ ውጭ ካጋጠመ ሌላ በሚለው አቅጣጫ የቤቱ ጣራ የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ተመዝግቦ በካርድ ኮሎም 34 ውስጥ ኮድ 7 ይሞላል፡፡

1 = ቆርቆሮ
2 = ኮንክሪት/ስሚንቶ
3 = እንጨትና ጭቃ
4 = ሣር
5 = ሸንበቆ
6 = አስቤስቶስ
7 = ሌላ /ይገለጽ———

<u>ዓምድ 47 የቤቱ ወለል አብዛኛው የተሠራው ከምንድን ነው ?</u>

አብዛኛው የቤቱ ወለል የተሠራበትን የሕንፃ ዕቃ ዓይነት በመጠየቅ ለተሰጠው መልስ ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝር ውስጥ በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በካርድ ኮሎም 35 ውስጥ ይሞላል፡፡ ከተዘረዘሩት ኮዶች ውጭ ካጋጠመ ሌላ በሚለው አቅጣጫ የቤቱ ወለል የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ይመዝገብና በካርድ ኮሎም 35 ውስጥ ኮድ 8 ይሞላል፡፡

0 = አፈር
1 = ሣንቃ
2 = ሲሚንቶ /ሊሾ/
3 = ፕላስቲክ ንጣፍ
4 = ስሚንቶ ሸክላ ንጣፍ
5 = ማርሞ ንጣፍ
6 = ድንጋይ
7 = ሸንበቆ ወይም ቀርቀሃ
8 = ሌላ ይገለጽ_______

<u>ዓምድ 48 አብዛኛው የቤቱ ክፍል ኮርኒስ አለው ወይ ?</u>

ኮርኒስ፡— ከቤቱ ጣራ በታች ትንሽ ዝቅ ብሎ የሚገኝ የቤቱ ወይም የክፍሉ የውስጥ ክዳን ኮርኒስ ይባላል፡፡ ኮርኒስ ከቤቱ ግድግዳ ጣራውን ከደገፈው እንጨት ፣ ብረት፣.... ወዘተ የተያያዘ ሲሆን በጨርቅ፣ በባንቧ፣ በኮንፓንሳቶ፣ በችፕ በርድ፣ በስሚንቶ.... ወዘተ ሊሠራ ይችላል፡፡

አብዛኛው የቤቱ ክፍል ኮርኒስ አለው ወይ ብሎ በመጠየቅ ለተሰጠው መልስ ቀጥሎ ከተዘረዘረው በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ክብ በማድረግ በካርድ ኮሎም 36 ውስጥ

ደገሞ ይኸው ኮድ ይሞላል፡፡ አንድ ክፍል ብቻ ኮርኒስ ኖሮት አብዛኞቹ የቤቱ ክፍሎች ኮርኒስ ከሌላቸው ቤቱ ኮርኒስ እንደሌለው ይቆጠራል፡፡

1 = አለው
2 = የለውም

## ዓምድ 49 ቤቱ ኮርኒስ ካለው አብዛኛው የቤቱ ኮርኒስ የተሠራው ከምንድን ነው?

አብዛኛው የቤቱ ኮርኒስ የተሠራበትን የዕቃ ዓይነት በመጠየቅ በተሰጠው መልስ ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝሮች ውስጥ በትክክለኛው ኮድ ክበ በማድረግ ይኸው ኮድ በካርድ ኮለም 37 ውስጥ ይሞላል፡፡ ከተዘረዘሩት ኮዶች ውጭ ካጋጠመ ሌላ በሚለው አቅጣጫ የቤቱ ኮርኒስ የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ይመዘገብና በዓምድ 49 በካርድ ኮለም 37 ውስጥ ኮድ 7 ይሞላል፡፡

1 = ወርቅ
2 = ኮምፔንሳቶ
3 = ቾኘ ካርድ
4 = ባንዳ
5 = ስሚንቶ
6 = ፋይዞት
7 = ሌላ ይገለጽ_______

## ዓምድ 50 ቤቱ ስንት ክፍሎች አሉት ?

"ክፍል" ሲባል ዙሪያውን ከወለል እስከ ኮርኒሱ ወይም ጣሪው ወይንም 2 ሜትር በሚደርስ ግድግዳ የተከበበና ቢያንስ አራት ካሬ ሜትር የሆነ ቦታ ሆኖ ሰፋቶ ለአንድ አዋቂ ሰው አልጋ ለማዘርጋት የሚበቃ ሥፍራ ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ጠቅላላ የቤቱ ክፍሎች የእንግዳ መቀበያ ቤሳን፣ የምግብ፣ የመኝታ፣ የወጥ ቤት፣ የሠራተኛ መኝታና ሌላ ሥራ የሚያገለግሉ ክፍሎችንም ያጠቃልላል፡፡ ነገር ግን የመታጠቢያና የመጸዳጃ ክፍል፣ የመተላለፊያ ኮሪደሮችና በረንዳዎች እንደ ክፍል አይቆጠሩም፡፡

ስለዚህ በዓምድ 50 በተሰጠው ክፍት ቦታና በካርድ ኮለሞች 38 እና 39 ውስጥ የክፍሎችን ብዛት መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ቤተሰብ ከአንድ ቤት በላይ ካለው በቤቶቹ የሚገኙት ጠቅላላ ክፍሎች በአንድ ላይ ተደምረው በዚሁ ዓምድ ይመዘገባሉ፡፡

1 = ማድ ቤት የለውም
2 = ዘመናዊ ማድ ቤት በግል
3 = ዘመናዊ ማድ ቤት በጋራ
4 = ባህላዊ ማድ ቤት በግል
5 = ባህላዊ ማድ ቤት በጋራ

**ዘመናዊ ማድ ቤት**

ቢያንስ የቧንቧ ውሃና የዕቃ ማጠቢያ /ሲንክ/ ያለውና እንዲሁም ለምግብ ማብሰያ ከኤሌክትሪክ ምድጃ፣ ከቡታ ጋዝ ምድጃ፣ የሰምበ ምድጃ፣ ከአንጨት ወይም ከከሠል የሚሠራ ዘመናዊ ምድጃ፣.... ወዘተ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ያለው ዘመናዊ ማድ ቤት ይባላል::

**ባህላዊ ማድ ቤት፣**

የቧንቧ ውሃና የዕቃ ማጠቢያ /ሲንክ/ የሌለውና አንጨት፣ ቁሬት፣ ከሰል፣ ቅጠል፣..... ወዘተ ለማገዶ በመጠቀም ምግብ ለማብሰል የሚያገለግል ባህላዊ ማድ ቤት ይባላል::

**ዓምድ 54 ቤቱ ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ ምን ዓይነት ማገዶ ይጠቀማል?**

የቤቱ ነዋሪዎች ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙበትን የማገዶ ዓይነት በመጠየቅ በተገኘው መልስ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የኮዶች ዓይነት በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 54 በካርድ ኮለም 46 ውስጥ ይሞላል::

1 = ኤሌክትሪክ
2 = ቡታ ጋዝ
3 = ኤሌክትሪክና ቡታ ጋዝ
4 = ኤሌክትሪክ አንጨትና ከሰል
5 = ቡታ ጋዝ አንጨትና ከሠል
6 = አንጨትና ከሰል /በጋቶሬና ቅጠል ይጨምራል/
7 = አንጨት /በጋቶሬና ቅጠል ይጨምራል
8 = ሌላ /ይገለጽ______

**ዓምድ 55 ቤቱ የመጠጥ ውኃ የሚያገኘው ከየት ነው ?**

በዚህ ዓምድ በቤቱ የሚኖሩት አባላት ለመጠጥና ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙበትን ውኃ ከየት እንደሚያገኙ በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተሰጡት ዝርዝር ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይሕው ኮድ በዓምድ 55 በካርድ ኮለም 47 ውስጥ ይሞላል።

0 = ከቧንቧ ውኃ አቤት ውስጥ
1 = " " ከግቢው ውስጥ በግል
2 = " " ከግቢ ውጭ በጋራ
3 = " " ከግቢው ውጭ ከቦኖ
4 = " " ከግቢው ውስጥ በጋራ
5 = " " ከግለሰብ /ከቋርፎት/ በነፃ፣ በግዥ
6 = ከተጠበቀ ጉድጓድ /ምንጭ/
7 = ካልተጠበቀ ጉድጓድ/ምንጭ/
8 = ወንዝ፣ ሐይቅ/ኩሬ/

ከላይ በኮድ "6" እና"7" የተመለከቱትን መልሶች በሚገባ ለይቶ ለማወቅ "የተጠበቀ የጉድጓድ/ምንጭ ውኃ" ትርጉሙን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

የጉድጓድና የምንጭ ውኃ አጠባበቅ ዘዴዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1/ በጉድጓድ ወይም በምንጩ ዙሪያ በቢሚንቶ የተገነባ ግንብ መኖር አለበት፣ ይኸውም:—

ሀ. ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ በሚገኝበት የአፈር ሁኔታ ግንቡ ቢያንስ ከ2 እስከ 4 ሜትር ወደ መሬት ውስጥ የገባ እና 70 ሳንቲ ሜትር ያህል ደግሞ ከመሬት ወደላይ የወጣ መሆን ይኖርበታል።

ለ. ምንጭ ከሆነ ግንቡ ዓለት እስከሚገኝበት ድረስ መሬት ውስጥ የገባና እንደ አስፈላጊነቱ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል። ከግንቡ በአንድ በኩል ውኃ ማውጫ ክፍት ቧንቧ ያለው መሆን አለበት፣

2/ በጉድጓድም ሆነ በምንጭ ዙሪያ የተገነባው ግንብ ከላይ ከሲሚንቶ የተሠራ ወይም ሌላ ዓይነት ጥብቅ ክዳን እንዲኖረው ያስፈልጋል፣

መጸዳጃ ቤት እንደሌለው ይቆጠራል፡፡

1 = መጸዳጃ የለውም
2 = በውኃ የሚወርድ መጸዳጃ የግል
3 = በውኃ የሚወርድ መጸዳጃ ለጋራ
4 = የጉድጓድ መጸዳጃ ለግል
5 = የጉድጓድ መጸዳጃ ለጋራ

ዓምድ 58 ቤቱ ምን ዓይነት መብራት አለው ?

ቤቱ ምን ዓይነት መብራት እንዳለው በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች ውስጥ በትክክለኛው ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 58 በካርድ ኮለም 50 ውስጥ ይሞላል፡፡

1 = ኤሌክትሪክ ቆጣሪው የግል
2 = ኤሌክትሪክ ቆጣሪው የጋራ
3 = ማሾ
4 = ፋኖስ
5 = ኩራዝ
6 = ሌላ /ይገለጽ/____________

ዓምድ 59 እዚህ ቤት ሬዲዮ አለ ?

የቤቱ ነዋሪዎች ሬዲዮ እንዳላቸው በመጠየቅ ቀጥሎ ከተሰጡት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 59 በካርድ ኮለም 51 ውስጥ ይሞላል፡፡

1 = አለ /ሬዲዮ አላቸው/
2 = የለም /ሬዲዮ የላቸውም/

ዓምድ 60 እዚህ ቤት ቴሌፎን አለ ?

በቤቱ ቴሌፎን እንዳለ በመጠየቅ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 60 በካርድ ኮለም 52 ውስጥ ይሞላል፡፡

1 = አለ /ቴሌፎን አላቸው/
2 = የለም /ቴሌፎን የላቸውም/

ዓምድ 61 እዚህ ቤት ቴሌቪዥን አለ ?

ቤቱ ቴሌቪዥን እንዳለው በመጠየቅ ቀጥሎ ከተሰጡት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 61 በካርድ ኮለም 53 ውስጥ ይሞላል፡፡

በታ ማጠቃለያ ቅጽ መተሳሰፍ የሚገባቸው መረጃዎች እንዲተሳሰሩ ይደረጋል፡፡

የቆጠራ ብታ ማጠቃለያ ቅጽ የሚሞላው በየቀኑ ቢሆን ይሻም የቆጠራ መጠይቅ መሞላት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ቆጠራው በቆጠራ በታው ውስጥ እስከ ተጠናቀቀ ድረስ ነው፡፡

ክፍል 1 <u>የአካባቢ መለያ</u>

ይህ ክፍል ቆጠራው ስለሚካሄድበት ቆጠራ በታ አድራሻ መመዝገቢያ የሚያገለግል ነው፡፡

<u>ዓምድ 1—3 ክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ</u>

የቆጠራ በታው የሚገኝበት ክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ ስም ከዓምድ 1—3 ቢተሰጡት ክፍት በታዎች ይመዘገባል፡፡

<u>ዓምድ 4—5 ከተማና ከፍተኛ</u>

የቆጠራ በታው የሚገኝበት ከተማ ስም በዓምድ 4 ተጽፎ የከፍተኛው ኮድ በዓምድ 5 በከርድ ኮለም 9 እና 10 ይመዘገባል፡፡ ከተማው ከፍተኛ ከሌለው በዓምዱ በከርድ ኮለም 9 እና 10 በሠረዝ " — " ምልክት ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ 6 የመቆጣጠሪያ በታ</u>

የቆጠራ በታው የሚገኝበት የመቆጣጠሪያ በታ ኮድ በዓምድ 6 በከርድ ኮለም 11 እና 12 ይመዘገባል፡፡

<u>ዓምድ 7 ቀበሌ ማኅበር</u>

ቆጠራ በታው የሚገኝበት የቀበሌ ማኅበር ስም በዓምድ 7 በተሰጠው ክፍት በታ ተመዝግቦ ኮዱም በከርድ ኮለሞች 13—15 ውስጥ ይሞላል፡፡

<u>ዓምድ 8 የቆጠራ በታ</u>

ቆጠራው የሚካሄድበት የቆጠራ በታ ኮድ በዓምድ 8 ከ16—17 ባሉት ካርድ ኮለሞች ይመዘገባል፡፡

## ክፍል 2 መሠረታዊ የሕዝብ ባሕሪያት ማጠቃለያ

ይህ ክፍል በቆጠራው ቦታ ስለሚኖሩት ሰዎች ብዛት በጾታ፣ ባለፉት 12 ወራት በቤተሰቡ የተወለዱ ልጆች ብዛት፣ ባለፉት 12 ወራት ከቤተሰቡ በሞት የተለዩ አባላት ብዛት፣ ማንበብና መጻፍ የማይችሉና የሚችሉ ብዛት፣ እንዲሁም የብሔረሰብ ዓይነትና ብዛት የሚመዘገብበት ነው፡፡ ክፍል 2 መሞላት ያለበት በቅድሚያ የቆጠራው መጠይቆች በተሟላ ሁኔታ መሞላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

### ዓምድ 9 የቤት ተራ ቁጥር

በሕዝብና በቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 10 የቤት ተራ ቁጥር ተሞልቷል፡፡ ስለዚህ በቅጽ 4 ዓምድ 9 በካርድ ኮለም 18 — 20 ላይ ለሚመለከተው ቤተሰብ የሚሞላው ቁጥር በሕዝብና መኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 10 የተሞላው የቤት ተራ ቁጥር ነው፡፡

### ዓምድ 10 የነዋሪው ዓይነት

በሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ በዓምድ 9 ካርድ ኮለም 23 የተሞላው የነዋሪ ዓይነት ኮድ በቅጽ 4 ዓምድ 10 ካርድ ኮለም 21 ላይ ይገለበጣል፡፡

### ዓምድ 11 የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር

በዓምድ 12 ለሚመዘገበ የነዋሪ ዓይነት ማለትም ለመደበኛ ቤተሰብ የቤተሰብ ኃላፊ ስም፣ ለሆቴልና ለሆስቴል ስም፣ መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች የሚያድሩበት ቦታ ስም በዚህ ዓምድ 001፣ 002፣ 003፣.... ወዘተ በማለት ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል፡፡

### ዓምድ 12 ስም

በዓምድ 10 በተገለፀው የነዋሪው ዓይነት ኮድና በዓምድ 11 በተገለፀው የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር አንጻር የተመለከተው መደበኛ ቤተሰብ ከሆነ የቤተሰብ ኃላፊ ስም፣ ሆቴልና ሆስቴል ከሆነ የሆቴሉና የሆስቴሉ ስም ሌላ ጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ከሆነ የጋርዮሽ መኖሪያ ቤት ስም፣ እንዲሁም መኖሪያ ቤት የሌላቸው ከሆነ የሚያድሩበት ቦታ ስም ይገለበጣል፡፡

ዓምድ 18 ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት፣

ቆጠራው በቆጠራው ቦታ ከተጠናቀቀ በኋላ በቆጠራው ቦታ ውስጥ የሚኖሩት ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት በቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ በዓምድ 18 በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ ብዛቱ የሚገኘው ከቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ ክፍል 2 ዓምድ 16 ሲሆን ይኸውም የመጨረሻውን የቤተሰብ ተራ ቁጥር በመውሰድ ይሆናል፡፡ በመመዝገቢያ ቅጽ የተገኘው የቤተሰቦች ብዛት በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ከተሞላባቸው የቤተሰቦች ብዛት መመሳከር አለበት፡፡ ካልተመሳከረ ግን የማጠቃለያው ቅጽ አሞላል ሁኔታ እንደገና በትክክል መፈጸሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 19 ጠቅላላ የመኖሪያ ቤቶችና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት

ቆጠራው በቆጠራ ቦታው ከተጠናቀቀ በኋላ በቆጠራ ቦታው ውስጥ ለመኖሪያ ብቻ እና ለመኖሪያና ለድርጅት የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት፣ በቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ በዓምድ 19 በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል፡፡ ብዛቱ የሚገኘው በቆጠራው ቦታ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ የተሞላባቸውን መኖሪያ ቤቶች ብዛት በመቁጠር ይሆናል፡፡ ይህም የሚገኘው በቤት፣ በቤተሰብና በድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ—1 ከተመዘገቡት መደበኛ መኖሪያ ቤትና መደበኛ መኖሪያና ድርጅት/በቅጹ በዓምድ 12 ኮድ "1" እና ኮድ "2" የተሰጣቸው/ የሆኑ ቤቶች ብዛት ጋር መመሳከር አለበት፡፡

ዓምድ 20 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ስም፣ ፊርማና ቀን

በመጨረሻም የቆጠራ የማጠቃለያ ቅጽ በትክክልና በተሟላ አኳኋን የተፈጸመ ስለመሆኑ ቆጣሪውና ተቆጣጣሪው በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ስማቸውን፣ ፊርማቸውንና ቀኑን ይሞላሉ፡፡

## ስለ ቆጠራ ቦታ ካርታ ዝርዝር መግለጫ

እያንዳንዱ ቆጣሪ ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት በተቆጣጣሪው አማካኝነት የተመደ በበትን የቆጠራ ቦታ ካርታ እና ስለ ቆጠራው ቦታ የሚገልጽ የቆጠራ ቦታ መግለጫ ጽሑፍ ይደርሰዋል:: እያንዳንዱ ቆጣሪ እነዚህ ሁለቱ ከደረሱት በኋላ ስለ ተመ ደበበት የቆጠራ ቦታ በይበልጥ ለመረዳት ካርታውን ማጥናት ይኖርበታል::

### ሀ. በገጠር የሚገኝ የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙበታል

1. የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ፣ ወረዳ እና ገበሬ ማኅበር ስም፣
2. የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት የገበሬ ማኅበር ሊቀመንበር ስም፣
3. የቆጠራው ቦታ መለያ ቁጥር /ኮድ/
4. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ብዛት፣
5. የቆጠራው ቦታ ግምታዊ ስፋት፣
6. የቆጠራ ቦታ ድንበር ከትክክለኛ ስሙና አቀማመጥ ጋር፣
7. በቆጠራ ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ መንደሮች ትክክለኛ አቀማመጥና ስማቸው፣
8. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ እና ድንበር አካባቢ የሚገኙ አንዳንድ ቤቶች፣ ወንዝ፣ የእርሻ ቦታ፣... ወዘተ
9. የቆጠራውን ቦታ የሚያዋስኑ ገበሬ ማኅበር ወይም ወረዳ ወይም ሌላ ቆጠራ ቦታ ስም፣
10. የቆጠራው ቦታ ሰሜናዊ አቅጣጫ፣
11. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ምልክቶች /ሌጀንድ/ በምሳሌ መልክ፣
12. የካርታው መስፈርት፣

### ለ. በከተማ የሚገኝ የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት አለበት

1. የቆጠራው ቦታ የሚገኝበት ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ እና ወረዳ፣
2. " " " የከተማ ስም፣
3. " " " ከፍተኛ እና ቀበሌ ቁጥር፣
4. በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ የቤቶች እና የቤተሰቦች ብዛት፣
5. የቆጠራው ቦታ ግምታዊ ስፋት፣

ክፍለ ሀገር ........ ሸዋ

አውራጃ ........... ጨቦና ጉራጌ

ወረዳ ............. ኢሉ


የገበሬ ማህበር ስም .... አሰንጎ

የሊቀ መንበር ስም ...... አበባው አሰፋ

የቆጠራ ቦታ ቁጥር ..... 14—01

የቆጠራ ቦታ ስፋት ...... 8 ኪ.ሜ²


የቤተሰብ ብዛት ......... 210




የቆጠራ ቦታ ቁጥር 14—02

መስፈርት 1:50,000

## መግለጫ



FORM R—5



# CENTRAL STATISTICAL OFFICE

## DESCRIPTION FORM FOR RURAL ENUMERATION AREA

1·REGION ሸዋ 2· AWRAJA ጨቦና፡ጉራጌ 3·WEREDA ክ.ሶ

4·EA· CODE № 14·01 5·NAME OF PAA/SUBDIVISION ሸበንጉ

6·PAA/SUBDIVISION CODE № 14

### DESCRIPTION OF THE EA·


DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE THE CIRCUIT CLOCKWISE

የሚዪዴውን፡ የእግር፡ መንገድ፡ ያድርጎና፡ የጉልባ፡ ገመዴን፡ ቤት
በውስጥ፡ የሚል፡ ባይን፡ ቤት፡ በሁሉም፡ በመደረግ፡ እስከ፡ ቀበሌ፡
ወንዝ፡ ድረስ፡ ይወሰናል

N.B. ATTACH THIS FORM TO FORM R - 4 USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED

NAME OF GA [illegible] INITIAL [illegible] DATE 19/9/73


NAME OF SUPERVISOR [illegible] INITIAL [illegible] DATE 20/9/73



ክፍለ ሀገር ---- ሸዋ
ከውራጃ ------ ሰሜን ጉራጌ
ወረዳ -------- ኪሉ
ከተማ -------- ተጂ
መስፈርት 1:40 00
01-01
01-02
መግለጫ
የገበሬ ማህበር ክልል
የቆጠራ ቦታ ክልል
አስፋልት መንገድ
የበጋ መንገድ
የማይደርቅ ወንዝ
ቤተ ክርስቲያን
ትምህርት ቤት
ቆርቆሮ ቤት
ሣር ቤት
ወፍጮ ቤት
ሀኪም ቤት
ቦኖ ውሀ
ድልድይ
H ሆቴል
A አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

| | |
|---|---|
| ክ/ሀገር ሸዋ | ከፍተኛ 1 |
| አውራጃ የረርና ከረዩ | ቀበሌ 07 |
| ወረዳ አዳማ | የቀ/ሊ/መ/ስም ፊቃዱ ሀብቴ |
| ከተማ ናዝሬት | የቆ/ቦታ ቁ/ 1-07-01 |
| | የቤቶች ብዛት 155 |
| | የቤተሰብ ብዛት 130 |

ከላይ የተዘረዘሩት በፋይል ( ከላሴር ) በስተጀርባ ተጽፈው ይገኛሉ




# መግለጫ

| | |
|---|---|
| (thick line) | መንገድ |
| (double line) | የገበሬ፡ ወሰን |
| (thin line) | የቆጠራ፡ ቦታ፡ ክልል |
| (hatched box) | ቤት |

1-07-01 የቆጠራ፡ቦታ፡መ/ቁጥር

FORM U—4

Page __ of __ pages

# CENTRAL STATISTICAL OFFICE

## FORM FOR DESCRIBING URBAN ENUMERATION AREA

1· REGION ሸዋ 2· AWRAJA የረርና ከረዩ 3· WEREDA አደማ

4· NAME OF URBAN CENTER ናዝሬት 5· KEFETEGNA 1 6· KEBELE 07

7· E·A· Nº 01

### DESCRIPTION OF THE E·A·

DESCRIBE THE IDENTIFIABLE BOUNDARIES FROM NORTH AND COMPLETE THE DESCRIPTION CLOCKWISE

በሰሜን ፦ የባቡር ሐዲድ ወሰን ሆኖ ያገለግላል

በምሥራቅ ፦ የኢትዮጵያ ትቅደም ጎዳና ወሰን ሆኖ ያገለግላል

በደቡብ ፦ በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በቀበሌ 07 ጽ/ቤትና በመጋዘን 344 ፊትለፊት በሚገኘውና ሰፊ ግልጽ የመኪና መንገድ ይዋሰናል

እነዚህ የጠቀስኳቸው ጽ/ቤቶች ሁሉ በቆጠራው ቦታ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው

ከቆጠራው ቦታ ክልል ውጪ የሚገኙት የከፍተኛ 1 ጽ/ቤትና መጋዘን 1 ናቸው

በምዕራብ ፦ ወሰኑ አለቃለት በሆነው የምንጃር ጎዳና ይዋሰናል

NAME OF E.A. ተሰማ ሁንዴማ INITIAL [illegible] DATE 8–4–74

NAME OF SUPERVISOR መኩብብ INITIAL [illegible] DATE 8–4–74


N.B. ATTACH THIS FORM TO FORM U-2 AND USE ADDITIONAL FORM IF NEEDED

ክ/ሀገር ሸዋ
አውራጃ የረርና ከረዩ
ወረዳ አዳማ
ከተማ ናዝሬት

የመቆጣጠሪያ ቦታ ቁጥር 05
የቆጠራ ቦታ ብዛት 6

ከላይ የተዘረዘሩት በፋይል (ከላሴር) በስተጀርባ ተጽፈው ይገኛሉ

በከተማ የመቆጣጠሪያ ቦታ ምስል




መፍቻ

1-07-01 የቆጠራ ቦታ ቁጥር
05 የመቆጣጠሪ ቦታ ቁጥር
—— የቆጠራ ቦታ ድንበር
—— የመቆጣጠሪያ ቦታ ድንበር

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመ በት ዓመተ ምሀረት | ድርጊቱ ከተፈጸመ በት እስከ 1976 ዓ.ም. ያለፉት አመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 54 | የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 9 |
| 55 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 9 |
| 56 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአረፉበት | 1967 | 9 |
| 57 | የእናት አገር ጥሪ የተደረገበት | 1969 | 7 |
| 58 | የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ አንደኛ ጉባኤ የተካሄደበት | 1972 | 4 |
| 59 | የኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. ሁለተኛ ጉባኤ የተካሄደበት | 1975 | 1 |